# ትግላችን

አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር
ወርሃዊ መፅሄት
በአውሮፖ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

## የቀኝ አድርባይነት

የመፅሄት አዘጋጅ ቦርድ፥
P.O.BOX 3198
103 64 STOCKHOLM 3
SWEDEN

ቁጥር ፩ የካቲት ፲፱፻፷፭

# መ ግ ቢ ያ

መቸም ቢሆን አድሃሪው ንጉስ ከበርቴ ተራ ብልጣ ብልጥነትን እንዳሁኑ ያጧጧፈበት ሰዓት ኖሮ ለማለት ያስቸግራል:: ፀረ አብዮተኛነትን በጥራዝ ነጠቅ ቲያሪው ለመሸፈን ሲል የሚያደርገው መገደርደር ይህ ነው አይባልም:: ደረቅን ሀቅ አራሱ በፈጠረው ውሸትና ሀሜት ለመተካት ሲል የሚያሰየው አይን አውጣነት ወሰን ጥሏል:: ይህ ሁሉ አልሆን ሲለው ደግሞ ሌላውን በጉልበት ለማንበርከክ ይሞክራል::

ወዝ ማሌሬድና ሰደዱ አንኳን በግልጽ የተቃወማቸውን ቀርቶ ተቃዋሚ የሚመስሳቸውን የግራ ድርጅትም ሆነ ግለሰብ አስቀድመው በአድርባይነት ይወነጅሉታል:: ነገሩ ሌባውን ሰዎች ሲያባርሩት አሱም ሌባውን ያዘው እያለ እን ደሚሮጠው አይነት ይመስላል:: አድሃሪው ቢሮክራሲም አንደአቅሚቲ በየደረሰበ ት ቦታ ''አድርባዮች''እያለ ተራማጆችን መሰየም ፈሊጥ አድርጉታል::

ትግላችን በዚህ እትሙ የንጉስ ከበርቴውን ተራ ብልጣ ብልጥነትና የቢሮ ከበርቴውን ድንፋታ ቀጋ ሳይሰጥ የአድርባይነትን መሰረታዊ ጠባዮች ለማ ሳየት ይሞክራል:: በበኩላችን ጽሁፉ በቂ ነው አንልም:: ሆኖም ግን ዛሬ በየቦታው አድርባዮችና የቢሮ ከበርቴው የሚያደርጉትን ተራ ወንጀምበር ለመቋቋሚ ያ አስፈላጊነትና ጠቃሚነትን አንጠራጠርም:: በተለይ የመንደር አሉባልታና የተኮላሸ ቲያሪ ለሰለቸው አንባቢ መሠረታዊ ለሆኑ ሳይንሳዊ ውይይቶች ጽሁፉ መድረክ ይከፍታል ባዮች ነን::

ት ግ ላ ች ን

ከመጋቢት ወር 1969 ዓ.ም ጀምሮ የኢት አብዮት አዲስ መስመርና አዲስ
አዝማሚያ እየያዘ መሄዱ ተደጋግሞ መነገሩ ብቻ ሳይሆን ዛሬ በኢት ውስጥ አፈር ቆ
ጠሉ በገልጽ የሚያየው ነው፡፡ በዚህ ከጊዜ ወደጊዜ በኢት አብዮት ውስጥ እያደገ
ና እየተጠናከረ በመሄዱ ላይ በሚገኘው የቀኝ አድርባይነት መስመርና በብሄራዊ ዲሞ
ክራቲክ አብዮት ፕሮግራም መሃከል ያሉት ቅራኔዎች ሊደበቁ የማይችሉበት ሁኔታ ላይ
ደርሰው የብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም የኢት ጭቁን ህዝቦች በስነት ትግ
ልና መስዋትነት ያገኟቸው ድሎች በአብዮት ስም እየተረገጡና እየተቀለበሱ በመሄድ
ላይ ይገኛሉ፡፡

ለጥቂት ጊዜም ቢሆን የዚህ መስመር አራማጆች ደርግ/ሰደድ፣ ወዝና ማሌሪድ
በፈረደባቸው በማርክስና በሌኒን እንዲሁም በብሄራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራም
ስም እየማሉና እየተገዘቱ ከዚህ በፊት ''ኢህአፓ''እንዳደረገችው በአብዮቱ ሰፈር
ና በሰፊው ህዝብ ውስጥ ይህ ነው የማይባል ውዥንብርን አሰራፍተው እንደነበረ አይ
ዘነጋም፡፡ እነርሱን የአብዮቱና የሰፊው ህዝብ አንደኛ ተዋርቷሪ መኢሶንና ሌሎች
ሃቀኛ ተራማጆችን አንደኛ የህዝብና የአብዮቱ ጠላት ሬበቸውን ማርክሲስት ሌኒኒስቶ
ች መኢሶንንና ሌሎች ሃቀኛ ማርክሲስት ሌኒንስቶችን ''ቀኝ መንገደኞች''አድርጉ
ለማቅረብ ያላደረጉት ጥረት የለም፡፡ እዚህ ላይ የቀኝ አድርባዮች የሚያሰሩፉት
ውዥንብር አከትሟል ለማለት አይደለም፡፡ ወይም እንደ ''ኢህአፓ'' ተጋልጠው የኢ
ትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች በሙሉ ፀረ—አብዮተኛነታቸውን ነቅተውባቸዋልም ብለን በሙሉ አ
ፉችን ለመናገርም አይደለም፡፡ ምንም እንኳን እነዚህ የቀኝ አድርባዮች ከሰፊው
ህዝብ ጋር ለመጠረቭ ተቀራርጠው የኢህአፓ እጣ እንደሚደርሰባቸው ለአንዲት ሴኮንድ
እንኳን ባንጠራጠርም ቅሉ ለጊዜውም ቢሆን የአብዮቱን አመራርና የመንግሥቱን መኪና
በእጃቸው ሥር በመያዛቸው በጭቁኑ ህዝብ ክንድ ከመደምሰሳቸው በፊት በዚህች በጭር
ጊዜ ውስጥ በኢት አብዮት ላይ ከደረሱት ጉዳት የበለጠ አጥፍ ድርብ ጉዳት ሊያደር
ሱ ይችላሉ፡፡ በተለይም ብአለም አቀፍ ደረጃ ባሳቸው ድጋፍ የተነሳ በበቂ ሳልነ
ቃው፡ ሳልተደራጀውና ሳልታጠቀው የኢት ሰፊ ህዝብ ከኢህአፓ አስር እጥፍ የበለጠ ጠ
ንካራ ጠላቶች እንደሆኑ መገንዘብ አስፈላጊ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ሰፊው ህዝብ እነዚ
ህን ጠላቶችን ለመደምሰስ ለኢህአፓ ከደረገው ዝግጅት በበለጠ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

ምንም እንኳን በመጠረሻ ድል የሰፊው ህዝብና የሃቀኛ አብዮታዊያኖች መሆኑ ቢታወቅም ቅሉ በአንድ በተወሰነ ወቅት የአድርባዮች መጠናከር ወይንም መዳከም ከሰፊው ህዝብ የነፃነት፣የድርጅትና የትጥቅ ዝግጅቶች ጋር ዳይሌክቲካዊ በሆነ መንገድ የተያያዘ ነው፡፡ እንዲሁም የአድርባዮች በአብዮት ውስጥ ወሽንብርን ማስፋፋት እድሚ ሊረዝም ወይንም ሊያጥር የሚችለው የአብዮቱ ሃይሎች ካሏቸው የዲሞክራሲ መብቶችና ሃቀኛ ተራማጆች ከሚያካሂዱት የማጋለጥና የርእዮተአለም ትግል መፋፋም ጋር ነው፡፡ ለምሳሌ ኢህአፖ የህዝቡ ነፃነት፣ድርጅትና ትጥቅ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ በነበረበት ወቅት በአብዮቱ ሰፈር ይህ ነው የማይባል ወሽንብር ልትነዛ እንደቻለችና ይህንንም በአብዮቱ ሃይሎች ላይ ያለውን ድክመት በመጠቀም በተለይም ነፃ ውይይትና የርዕዮተ አለም ትግል በግልጽ በመንግሥቱ ዜና ማሠራጫዎች ለማካሄድ ባልተፈቀደበት ወቅት፣የሰፊውን ህዝብ የዲሞክራሲ መብቶች መታፈን ተገን አድርጋ ለጊዜውም ቢሆን ''ሃያል''መስሳ ለመቅረብ እንደቻለች አይዘነጋም፡፡ በዚያን በጭለማ ወቅት በማርክስና ሌኒን እየማለች ከላአኔ በስተቀር ማንም አብዮታዊ የለም በማለት ስንቱን የጭቁን ህዝብ ወገን እንዳወናበደችውና በዚያን ሰዓት በነበረው ዝቅተኛ የነቃት ደረጃ ስንቱ አምና እንደተቀበላት በኢት አብዮት አጭር ታሪክ ውስጥ ሶስት አመት እንኳን አልሞላውም፡፡ የዚያን ያህል ሃያል መስላ ሶንት የደነፋችው ኢህአፖ በተለይም በሰፊው ህዝብና በሃቀኛ ተራማጆች ትግል በዚያን ወቅት በተገኘው የዲሞክራሲ ጭላንጭል በመንግሥቱ የዜና ማሠራጫዎች ገልጽ ውይይት መካሄድ በጀመረበት ጊዜ መኢሶንና ሌሎች ተራማጆች ባካሄዱት የርዕዮተ አለም ትግል የ''ኢህአፖ'' ቀልባሽነት፣የመፈክሮቿ ትጥቅ አስፈችነት፣በአጭር ጊዜ ውስጥ በቀላሉ ተጋልጦ ሰፊው ህዝብ እንቅር ሊተፋት ችሏል፡፡ ''ኢህአፖ''ም በመጠረሻ በርዕዮተ አለም ትግል ከተሸነፈች በኋላና ሰፊውን ህዝብ በአብዮትና በሶሻሊዝም ስም ለማወናበድ ባለመቻሏ በሰፊው ህዝብ ክንድ እስከትደመሰስ ድረስ ከሰፊው ህዝብ አብዮት ቀንደኛ ጠላቶች ጋር ተሰልፋ አቅሟ የፈቀደላትን ያህል በአብዮቱ ላይ ጉዳትን አድርሳለች፡፡

ዛሬ በኢት ውስጥ ማንም ሰው አይኑን ጨፍኖ ራሱን ሳታል እስካላለ ድረስ ለሰፊው ህዝብ የነቃት ደረጃ ለማመን በሚያስቸግር ሁኔታ ከመቅጽበት ከፍ ሳማለትና ለኢህአፖ የገራ አድርባይ መስመር በአጭር ጊዜ ውስጥ ተንኮታኩቶ ለመውደቅ አመች ሁኔታን የፈጠረው በወቅቱ የነበረው የዲሞክራሲ ጭላንጭል መሆኑ ገልጽ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ነው ዛሬ የቀኝ አድርባዮች ደርግ/ሰደድ፣ ወዝና ማሌሪድ የዲሞክራሲ



ጥያቄ እንደጦር የሚፈሩት፡፡ [በነገራችን ላይ ምንም እንኳን ገልጽ ቢሆንም ለአነባቢያቻችን ለማስሰብ የምንሻው እኛ እስከምናውቀው ድረስ በደርግና በአብዮታዊ ሰደድ መሃከል በስም እንጂ በይዘት ልዩነት የለም፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ደርግን የሚመለከት ጥያቄ አብዮታዊ ሰደድን እንዲሁም ሰደድን የሚመለከት ጥያቄ ደርግን ይመለከታል] ለጊዜውም ቢሆን እንደ ኢህአፖ በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ወሽንብርን በአብዮቱ ሰፈር ሊያስፋፉና በአብዮቱም ላይ በየጊዜው ጉዳትን ሊያስከትሉ የቻሉት የሰፊው ህዝብ የነፃነት፣ የድርጅትና የትጥቅ ዝግጅት አሁንም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ በመሆኑና በተለይም የአብዮቱ አመራር በእጃቸው ስር በመሆኑ የሰፊውን ህዝብ የዲሞክራሲ መብቶች አፍነው በመያዝ ነው፡፡

ከዚህ ሌላ ያሁኑን ሁኔታ ከበፊቱ ትንሽ ለየት የሚያደርገው ነገር ቢኖር የ''ኢህአፖ'' ''የገራ አድርባዮች''በመንግሥቱ ጋር የነበራቸው ግንኙነትና የአሁኖቹ የቀኝ አድርባዮች ያላቸው ግንኙነት መሃከል ያሉት ልዩነቶች የፈጠሯቸው ልዩ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ ምንም እንኳን ኢህአፖ በደርግ ውስጥ ብዙ ደጋፊ ቢኖራትም ቅሉ፣ በጠቅላላ አድሃሪውን ቢሮክራሲ ብትይዝም ቅሉ ባጠቃላይ ደርግን በጁ ልታሰልፍ አልቻለችም ነበር፡፡ በደርግም ውስጥ የወቅቱ ተራማጅ ሃይሎች ከአድሃሪያችና ከኢህአፖ ደጋፊዎች ጋር ባካሄዱት ትግል ለጊዜው አሸንፈው ደርግ በመስከረም 68 በኢህአፖ ላይ አብዮታዊ አቋም ከመውሰዱ በፊት ደርግ በዚህ የርዕዮተ አለም ትግል ውስጥ ገለልተኛ ስለነበረ ሰፊው ህዝብ ያስተባሰብ ነፃነት ነበረው፡፡ እንደዛሬው የቀኝ አድርባዮች የመንግሥቱን የጭቆና መሣሪያዎች በመጠቀም በማሰር፣ በመግደል፣በማሰቃየት፣ ከሥራ በማባረር፣ የመኢሶንን አቋም ከለመንገዘብ የኛን አቋም አይንህን ጨፍነህ ካልተቀበልክ እያሉ ሳያስፈራሩትና ሳያስገድዱት በተራማጅ ልሳናችን፣በዜና ማሰራጫዎች፣ በጥናትና በውይይት ክበቦች ወዘተ...ከተካሄዱት ገልጽ የርዕዮተ አለም ትግል ነቃቱን አዳብሮ በገልጽ ማን፣አድሃሪ ማን፣ተራማጅ ማን፣የሱ ወገን ማን፣የአብዮቱ ጠላት መሆኑን ተረድቶት አብዮታዊ ፍርዱን በመስጠት ኢህአፖን ከነአድሃሪ መፈክሮቿ በማውገዝና አሽቀንጥሮ በታሪክ ትቢያ ውስጥ በመጣል የመኢሶንንና የሌሎች ሃቀኛ ተራማጆችን መፈክሮች በማንገብ ትግሉን ወደፊት አራምዷል፡፡ ዛሬ በቀኝ አድርባዮችና በማርክሲስት ሌኒኒስቶች መሃከል በሚደረገውን የመሥመር ትግል ከበፊቱ ልዩ የሚያደርገው የቀኝ አድርባዩ መስመር ደጋፊውና አራማጅ ራሱ መንግሥቱ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በዚህ የመስመር ትግል ውስጥ ሰፊው ህዝብ የመናገር ቀርቶ ያስተባሰብ እንኳን ነፃነቱ መነፈጉ ጭምር ነው፡፡ በተለይም በዚህ የርዕዮተ አለም ትግል ውስጥ መንግሥቱ ከሚከተለው የማንአለብኝነት የፀረ—አብዮት የ

የጭፍጨፋና የማስፈራራት ፖሊሲ ለጊዜውም ቢሆን በሰፊው ህዝብ ዘንድ የፈጠረው መሸ
በር፣መፈራራት፣ አለመተማመን ወዘተ...ገልጽ አብዮታዊ አቋም እንዳይወስዱ አገደታ
ል:: በአሁኑ ጊዜ ከመሞት መሰንበት ይሻላል በሚል ሳይወዱ በግድ ከመታሠር፣ከመ
ገደል፣ከመሰቃየት ለመዳን የሰደዱ አባል የሆነው ቁጥር ስፍር የለውም:: ''ኢህአ
ፖ''እያወናበደች የሰበሰበቻቸውን አባሎቿንና ጀሌዎቿን በፈላጭ ቆራጭነት አይናችሁ
ን ጨፍናችሁ እኔ አምላውን ተቀበሉ ትል እንደነበረና ከሷ አስተሳሰብ ውጭ የሆነው
ን ትገድል፣ትደበድብ እንደነበረ ሁሉ ዛሬም የቀኝ አድርባዮች የሚያደርጉት ይህንኑ
ነው:: ከኢህአፖ ጋር የሚለያዩበት ነገር ቢኖር የቀኝ አድርባዮች መንግሥቱም በ
ቁጥጥራቸው ሥር ስላሆነ የአስተሳሰብ ነፃነቱን ገፈው የፈላጭ ቆራጭነት ሥራ የሚያ
ከሄዱበት ለእንጀራ ሲል በየመሥሪያ ቤቱ ፎርሙን እየሞላ በተጠራቀመው አባላቸው ብ
ቻ ሳይሆን በጠቅላላው በኢት ሰፊው ህዝብ ላይ ጭምር መሆኑ ነው::

የግራና የቀኝ አድርባይነት በቅርጽ ይለያያሉ እንጂ በይዘት አንድ ናቸው::
ሁለቱም ፀረ—ህዝብ፣ ፀረ—አብዮት፣ፀረ—ወዝአደርና ፀረ—ሶሻሊስት ናቸው:: ሁለቱ
ም የሚያወናብቱት በሶሻሊዝምና በወዝአደሩ ስም ነው:: ሁለቱም እስከተወሰነ ደረ
ጃ ድረስ ሊያወናብቱት ከሚችሉት ሰፊ ህዝብ ጋር ሊያወናብቱበት ከማይችሉት ደረ
ጃ ላይ በሚደርሱበት ጊዜ ከሰፊው ህዝብ ጋር የማይታረቅ ቅራኔ ውስጥ ይገባሉ::
በመጨረሻም ከአብዮቱና ጠላቶች ጋር በግልጽ ተሰልፈው በሰፊው ህዝብ ላይ ያምጻሉ::

ይህ በአውሮፖ የኢት ተማሪዎች ማህበር ያወጣው ህግ ባይሆን በማንኛቸውም
አብዮት በተካሄደባቸው አገሮች የታየና የአብዮትን እድገት ህግ ተከትሉ የማይቀር
ሃቅ ነው:: ለዚህ ምሳሌ ለመፈለግ ከኢት ሶቭየት ህብረት ወይም፣ቻይና፣ወይም
አልባኒያ ሳንሻገር በኢት አብዮት በአጭር እድሜ ውስጥ በ ''ኢህአፖ''ላይ ታይቷ
ል:: የ ''የኢህአፖ''፣ ''የግራ አድርባይ''የፖለቲካ መስመር በአለም አቀፍ
ደረጃ የግራ አድርባዮች ከሚያራምዱት መሥመር ጋር በመሠረቱ አንድ እንደመሆኑ መጠ
ን ዛሬም በኢት ውስጥ የቀኝ አድርባዮች የሚያራምዱት ፀረ—ወዝአደር፣ፀረ—አብዮትና
ፀረ—ሶሻሊስት መስመር በአለም አቀፍ ደረጃ በወዝአደሩ ንቅናቄ ውስጥ ከታወቀው የ
ፀረ—ማሌ የቀኝ አድርባይ መስመር ሙሉ ለሙሉ በይዘቱ አንድ ነው:: ምንም እንኳ
ን የቀኝ አድርባዮች በኢትም ውስጥ ሆነ በሌሎች ቦታዎች እንደታየው የማሌ መሠረተ
ሃሳቦች የሚቀበሉ መስለው ለመቅረብ ቢሞክሩም ልክ በሌሎችም ቦታዎች የቀኝ አድርባ
ዮች እንደሚያደርጉት ማርክስና ሌኒን በሆነውና ባልሆነው እያጣመሙ እያቆላመሙ ቢጠ
ቅሱም በማርክሲዝም ሌኒንዝምና በቀኝ አድርባይነት መሃከል ያለው ልዩነት በአብዮት



ና በፀረ—አብዮት መሃከል ያለ ልዩነት ነው:: ታዲያ ይህን ያህል የሰማይና የመ
ሬት ልዩነት ካለ ለምን ማርክሲስቶች መስለው ለመቅረብ ይሞክራሉ ብሎ አንዱ ሰው
ይጠይቅ ይሆናል:: መልሱ ግን ብዙ የሚያከራክር አይደለም:: በተቀዳሚ ደረጃ
በሰፊው ህዝብ ዘንድ ተራማጅ አብዮታዊ መስሎ በመቅረብ ሰፊውን ህዝብ ለማወናበድ
ሲሆን፣ ሁለተኛ ሌኒን እንደሚለው "The developmen of science is
providing more and more material that proves that Marx was
right. This makes it necessary to fight against him hypocriti-
cally not to oppose the principles of Marxism openly, but to
pretend to accept Marxism, which emasculating it by sophistry
and turning it inte a holy "icon" that is harmless to the
bourgeoise." Lenin Col. Vol. 21 p. 223

''የሳይንስ እድገት በየጊዜው የማርክስን ትክክለኛነት እያረጋገጠ ይሄዳ
ል:: ስለሆነም ማርክሲዝምን ለመታገል የግድ አስመሳይ መስለው መቅረብ ይገደዳ
ሉ:: ማለትም የማርክስን መሠረተ ሃሳቦች በግልጽ እየተቃወሙ ሳይሆን ላይ ላዩን
ማርክሲዝምን የተቀበሉ በማስመሰል፣ ለማስመሰልና በሚያቀርቧቸው ክርክሮች ግን ማር
ክሲዝምን አኮላሽተው ከበርቴውን ወደ የማይጎዳ የተቀደሰ ''የአምልኮ ስእል''
ይቀይሩታል::

ለዚያም ሆነ ለዚህ በማርክሲዝም ሌኒንዝምና በቀኝ አድርባይነት መሃከል
ያሉትን መሠረታዊ ልዩነቶች እንመልከት:—

## ቀ ኝ  አ ድ ር ባ ይ  ስ ን ል  ም ን  ማ ለ ታ ች ን  ነ ው

ባጠቃላይ አነጋገር በወዝ አደሩ እንቅስቃሴ ውስጥ አድርባይነት ማለት በሶ
ሻሊዝምና በወዝ አደሩ ስም የሚነገድ በተግባር ግን የወዝ አደሩን መደብ አምባገነ
ንነት፣ የወዝአደሩን ጥቅም የማርክሲዝም ሌኒንዝምን መሠረታዊ ሃሳቦችና ሃቆች በከ
ፍተኛ ደረጃ የሚፃረር መስመር ማለት ነው::

የቀኝ አድርባይነትን አይነተኛ ከሚያደርጉት ፀረ—ማሌ አቋሞች ዋና ዋናዎቹ:-

— የወዝአደሩን መደብና የሶሻሊዝምን መሠረታዊ አላማዎች መካዳት
— የህገ ወጥ የትግል ስልትን ማንቋሸሽና አለመቀበል

— በህጋዊ የትግል ስልት ላይ ብቻ ማተኮር
— የማሌን መሠረታዊ ሃሳቦች የፕሪንስፕል ጥያቄዎችና አጠቃላይ ሃቶች ጀኔራል ትሬዝ መከለስ
— ማርክሲዝም ሌኒንዝምን በመከለስ በማጣመም ከአብዮታዊ ይዘቱ በመለየት ለአድሃሪያዎችና ለገዥ መደቦች መሣሪያ ለማድረግ መሞከር
— በሶሻሊዝም ስም ትምክህተኝነትን ማስፋፋት
— አብዮታዊ ስምምነቶችን ማፍረስና መከዳት
— በከበርቴው ላይ እምነት ማሳደርና በአብዮት ሠሪው በወዝ አደሩ ላይ እምነት ማጣት
— ከአብዮቱና ከሰፊው ህዝብ ጠላቶች ጋር የመደብ እርቅ ማድረግ
— የመንግሥትን [አስቴት] የመደብ ጠባይ ወይንም ይዘት አለመመልከት
— በሰላም ወቅት ከአድሃሪያዎችና ከአብዮቱ ጠላቶች ጋር በሥውር የሚያደርጉትን ትብብር በጦርነትና በቀውጢ ወቅት ይህን የድብቅ ትብብር በግልጽ አውጥቶ ከአብዮቱ ጠላቶች ጋር በቀጥታ አብሮ መሠለፍ
— በወሳኝ የትግል ወቅቶች ሰፊውን ህዝብ የሚያወናብቱ መፈክሮችን ማንሳት ናቸው::

በአለም አቀፍ ደረጃ የቀኝ አድርባይነት በወዝ አደሩ እንቅስቃሴ ውስጥ በመጀመሪያ መታየት የጀመረው ካፒታሊዝም አድጎ ኢምፔሪያሊዝም የእድገት ደረጃ ላይ በደረሰበት ጊዜ ነው:: በፕሮዳክሽን ክሬይስስና በወዝ አደሩ ትግል ተወጥሮ የነበረው የከበርቴ ስርአት ከ1871—እስከ 1914 በአፍሪካ፣በእስያና በላቲን አሜሪካ ኮሎኒያችን በመያዝና በነዚህ ሥፍራዎች የሚገኙትን ጥሬ እቃዎች በመዝረፍ ህዝቦችን በመበዝበዝ በተገኘው አዲስ ገበያ አንዳንድ ጥቃቅን የጥገና ለውጦችን ለማድረግ በመቻሉ በዚህ በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ በተገኘው ጊዜያዊ ''የሰላም''ወቅት የቀኝ አድርባይነት በወዝአደሩ እንቅስቃሴ ውስጥ መጀመሪያ በአዝማሚያ[ሙድ] መልክ ብቅ አለ:: ከዚያም ከአዝማሚያ ወደ አቅጣጫ[ትሬንድ]በመጠረሻም የወዝ አደሩን መስፍንትና የንዑስ ከበርቴ አጨፋሪዎችን ወደያዘ ቡድን ተቀየረ:: የዚህ ቡድን ተጠሪዎች የወዝ አደሩን አብዮታዊ አላማና ታክቲክ በአፍ ብቻ የተቀበሉ በማስመሰል የወዝ አደሩን እንቅስቃሴ በቁጥጥራቸው ስር አደረጉ:: የዚህን ቡድን ተጠሪዎች በሰፊው ህዝብ ውስጥ ለጊዜውም ቢሆን ተቀባይነት ሊያገኙ የቻሉት በካፒታሊዝም ሥርአት ውስጥ ከከበርቴው ጋር ባደረጉት ትብብርና የነሱ ''ሰላማዊ ትግል''በመጠረሻው



ለወዝ አደሩ አብዮት ዝግጅት ጠቃሚ ነው የሚለውን አስተሳሰባቸው ሊያሳምኑት በመቻላቸው ነው:: ሆኖም በዚህ የማጭበርበር ዘዴ እስከመጠረሻው ሊዘልቁበት አልቻሉም:: የኢምፔሪያሊስቶ ከበርቴ በኩሉ ሽሚያ እርስ በርሱ ተጋጭቶ የአንደኛ አለም ጦርነት በጀመረበት ወቅት በቀጥታ የወዝ አደሩን ጥቅምና የሶሻሊዝምን መሠረታዊ አላማ በመክዳት ከከበርቴው ጋር ጎን ለጎን ተሰልፈው ወዝ አደሩ ከአገሩ ከበርቴ ጋር ተሰልፎ በሌላው ወዝ አደር ማለትም የገዛ መደቡን እንዲዋጋ ቀሰቀሱ:: የዚህ ቡድን ተጠሪዎች በዚህ ወቅት እንደ እንግሊዝና ፈረንሳይ ለከበርቴው ባሳዩት ታማኝነት በአስተዳደር ካቢኔ ውስጥ እየተመለመሉ ገቡ:: እንደ ጀርመንና ራሺያ ያሉ አገሮች እንቅፋት ህጋዊ ህልውናቸው ታወቀላቸው:: በቁጥጥራቸው ሥር የያዟቸውም አድርባይ ፖርቲዎች በጦርነቱ ወቅት ከአገራቸው ከበርቴዎች ጎን ተሰለፉ::

## <u>አ ብ ዮ ት ና መ ን ግ ሥ ት</u>

አስቀድመን እንደተናገርነው አድርባዮች እንደማንኛውም የአብዮት ጥያቄ ይህን ጥያቄ ከማድበስበስና ከመሸሽ አያልፉም:: የተገደዱ እንደሆነ ደግሞ ጥያቄውን ባጠቃላይ መልኩ ብቻ አውርተውት ከማለፍ በስተቀር ተጨባጭ አድርገው ለማውራት አይወዱም:: የወዛደሩ አብዮት በግድ የገቻውን መደብ የመንግሥት መኪና ደምስሶና የራሱን አምባገነንነት መመሥረት እንዳለበት አይቀበሉም:: ተቀብለናል ቢሉም እንዴት ይመሠረታል ለሚለው ጥያቄ ግልጽና ትክክለኛ መልስ አይሰጡም:: የወዛደሩን አምባገነንነት ብቻ ሳይሆን ህዝባዊ ሥርዓትን በመገንባቱም ጥያቄ ላይ ያላቸው አቋም ይኸው ነው::

ታሪክ በዚህ ጥያቄ ከጊዜው ጋራ የዳበሩ ልዩ ልዩ የአድርባዮችን አቋም
መዝግቧል:: ማርክስ ''ወዛደሩ ያለውን የመንግሥት መኪና ተቀብሎ ሊገለገልበት
አይችልም'' ብሎ የተናገረውን በርንስታይን ተከታዮች እንደፈለጉት እየተረጐሙና
እያጣመሙ ያሸፉበት ዘመን ነበር:: በኋላም እነካውትስኪ የነበርንስታይንን አብ
ባል በረቀቀ መንገድ መልክ ለማስያዝ ሲሉ ''ጥያቄው ወደፊት የሚሆን ነገር ነው
ና ለጊዜው እንተወው''ያሉበትም ዘመን ነበር:: ቢሮክራሲውን ሰይመታ ወዛደሩ
በቍጥጥር ሥር አውሎ መጠቀም ይቻላል የሚል ፈሊጥም ታይቷል::

አድርባዮች በጠቃላይ አነጋገር አብዮት አዳካሚና አረጂም ነው እያሉ በነ
ልጽ ያወራሉ:: በአጠቃላይም ለወዛደሩና ለሰፊው ህዝብ ዱል ቆመናል ይላሉ::

አብዮት ማዳከሙና መርዘሙ ሀቅ ነው:: ገን አብዮትን አረጂምና አዳካሚ
ያደረጉትን ነገሮች በሚገባ አፍርጠው አያስዩም:: በተለይ የአብዮት እምብርት
ጥያቄ የሆኑትን ነገሮች <u>የመንግሥት ሥልጣን ጥያቄ</u>፣ አብዮትን ለምን አዳካሚና አ
ረጂም እንደሚያደርጉት ደፍረው አያነሱም:: በተለይ ካፒታል ዓለም አቀፋዊ በሆ
ነበት ዘመን፣ የብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮትና የሶሻሊዝም አብዮት እንደሰንሰለት
መያያዝ ባስፈለገበት ዘመን የመንግሥትን ጥያቄ ለምን አብዮትን አዳካሚና አረጂም
አደረገው? ለዚህ ጥያቄ አድርባዮች የሚሰጡት መልስ ቢኖር ከማርክሲዝም ሌኒኒዝ
ም መሠረታዊ ሃሳቦች የራቀ ታሪክና ቲዎሪ የማይደገፉቸው የተለያዩ መልሶችን
ነው:: ነገር ገን የነኚህ መልሶች ሺህ ጊዜ የተለያዩ ቢሆኑም በጋራ አንድ ዓ
ላማ ይይዛሉ:: ሁሉም ዓይነት መልሶች በሰፊው ህዝብ ጉልበትና የመፍጠር ችሎታ
ላይ ያልተማመኑ፣ ከኢምፔሪያሊዝም ጋራ ቁርጥርጥ ያለ ጠብን በቀጥታም ሆነ በተዘ
ዋዋሪ የማይሹ፣ በቢሮክራሲው ላይ ፍቅር ያላቸው፣ በከበርቴውና በንዑስ ከበርቴው
ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ሆነው እናገኛቸዋለን:: ከነካውትስኪ እንስቶ የዉሮፖ
ሶሻል ዴሞክራቶችና የወዛደሩ መሰፍንቶች አቋራርጦ በገራችን ያሉትን የወዛደር
መሰፍንቶችና አድርባይ ንዑስ ከበርቴዎች በንመለከት ይህን ሀቅ በጋራ ሲሸሙ
እናገኛቸዋለን:: ለዘላቂው ዱል ካለመቆማቸው የተነሳ የጠቀሳሳውን ሰፊ ህዝብ
ጉልበትና የመፍጠር ችሎታ ይፈራሉ:: ''ሃያሉ''ዓለም ዓቀፍ ኢምፔሪያሊዝምና



የውስጥ ተባባሪዎቻቸው [ቢሮክራሲው]የሚያደርጉትን ፀረ—ህዝብ አመጽ በሰፊው ህዝ
ቡ ሙሉ ተሳትፎ አንጂ ባለው ቢሮክራሲና በነሱ ሃይልና ጉልበት እንዳልሆነ በፍጹ
ም አይቀበሉም:: ዘር ዘር የምናየው ነገር ቢኖር አድርባዮች አብዮት አረጂምና
አዳካሚ ነው የሚለውን ሀቅ ይዘው በጣም ከረጅሙና ከአዳካሚው አውነተኛ የህዝ
ብ ትግል ጋራ ዝምዶና እንደሌላቸው ነው:: ያልነውን ሀቅ ሰያሟሉ ምንን ይዘ
አብዮት ይደረጋል? አብዮትን አዳካሚ ከሚያደርገው ቀነኛው የሆነው የመንግሥት
ሥልጣንን ጥያቄ ከቢሮክራሲውና ከአለም ዓቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ጋራ የለየለትን መቆ
ራረጥን ከጠየቀና፣ ይህም ደግሞ የሚቻለው በሰፊው ህዝብ አውነተኛ ተሳትፎ ብቻ
ከሆነ ከዚህ መንገድ ውጪ የሆነ ለውጥ መሠረታዊ የህብረተ ሰብ ለውጥ ሊሆን ፈጽ
ም አይችልም:: ከሆነ ሊሆን የሚችለው ጥገናዊ ለውጥ ብቻ ነው:: የአ
ድርባዮች አንቀ ጠባይ ማለት ነው::

አድርባዮች በመንግሥትና ጥያቄና በአብዮት መኻል ስለሚኖረው ግኑኝነት በ
ሳቸው ስህተተኛ አቋም የተነሳ ያለው አድሃሪ የመንግሥት መኪና በአዲስ የህዝብ
ሃይል መተካት እንዳለበት አይቀበሉም:: አንዳንድ ቦታ በፕሮግራም ደረጃ ቢቀበ
ሉትም በተግባር የሚመነዘርበትን መንገድ አጥብቀው ይቃወማሉ:: በመንግሥትና በ
ላዕላይ መዋቅሩ መኻል የፀና ግኑኝነት እንዳለ ይስታሉ:: ከዚህም የተነሳ የጥ
ገና ለውጥን እንደጣዖት ማምለክ ያዘወትራሉ:: ባሉት የጥገና ለውጦች በመጠቀም
በሰላም ወደ ሶሻሊዝም መሸጋገር ይቻላል ይላሉ:: ያሉትን የጥገና ለውጦች ሁል
ጊዜ የሚያነፃጽሩት ከቀደሞ ጥገና ለውጦች ዘመን ጋራ ወይም የጥገና ለውጡ ካልተ
ገኙባቸው ቦታዎች ጋራ ነው:: ለምሳሌ የከበርቴውን ዴሞክራሲ ለማድነቅ ሲሉ
ከፊውዳሉ ጋራ ብቻ አወዳድረው ቀጭ ይላሉ:: ነገር ገን አንዱ አርምጃ ወደፊት
ሄደው ከከበርቴው ዴሞክራሲ የህዝብ ዴሞክራሲ እንደሚበልጥና ለዚህም መታገል እን
ደሚያስፈልግ በተጠባጭ አይታገሉም:: እርገጥ ነው በሪፎርምና በአብዮት መኻል
ግኑኝነት አለ:: ለሰፊው ህዝብ ትግል የከበርቴው ዴሞክራሲ ሆነ ሌሎችም ሪፎር
ሞች እስከተወሰነ ደረጃ ይጠቅሙታል:: ያስፈልጉታልም:: ገን ይህ ማለት አድ
ርባዮች እንደሚሉት አብዮትን በሪፎርም የምንለውጥበት ደረጃ ያደርሰናል ማለት
አይደለም:: ሊሆንም አይገባውም:: ማርክሲስቶች ከቀኙም ሆነ ከግራ አድርባዮ
ች የሚለያቸው አንዱ መሠረታዊ ምክንያት ሪፎርምን ለአብዮት ተቀጥያና መገልገያ
ለማድረግ መቻላቸው ነው:: እንደቀኝ አድርባዮች በሪፎርም ሳያመልኩ፣ እንደግራ
አድርባዮች ፀረ—ሪፎርም ሳይሆኑ መራመድ መቻላቸው ነው::

ዛሬ በዚህ በሪፍርም ጥያቄ የሪፍርም አምሳኪያችንም ሆነ ፀረ—ሪፍርሚስት ድርጅቶችን ለቅሞ ለማስየት ከኢት ርቆ መሄድ አያስፈልገንም:: ከወዝና ከማሌሪዶ የበለጠ የቀኝ አድርባይ ከኢህአፖ የበለጠ የግራ አድርባይ በዚህ የሪፍርም ጥያቄ ላይ ለጊዜው አያስፈልገንም:: እንደነበርነስታይንና ተከታዮቻቸው ወይም እንደዘመኑ ኢዩሮ ኮሚዮኒስቶች በግልጽ ሪፍርሚስት መሆናቸውን በፕሮግራማቸው ላይ አሳስፈሩም ክብሎ ጥያቄ ሊቀርብ ይችል ይሆናል:: አዎ አሳሰፈሩም:: የአድርባይነትን መሥመር ለማየት ግን የነሱን ፕሮግራም ብቻ በመርመር አንወስንም እንላቸዋለን:: በኢት ያራመዱትና የሞሉት የፖለቲካ መሥመር ለአድርባይነታቸው በቂ ማረጋገጫቸው ነው:: የቀኝ አድርባዮች የሞሉት ፖለቲካ ምን ይነው?

አዎ! በዚህ አገር ያለው ነጥብ ለማስየት በዲሞክራሲ ጥያቄ ላይና በቢሮክራሲው ላይ ያላቸውን አቋም ማስየት ይበቃል:: በቂ ዲሞክራሲ አለ፤ ያለውንም ዲሞክራሲ ሰፊው ህዝብ ሊጠቀምበት አልቻለም፤ አሁን ዲሞክራሲ ቢለቀቅ አድሃሪው ነው የሚጠቀምበት፤ አገራችን በጦርነት ላይ እያለች ዲሞክራሲ አይጠየቅም፤ ከገዥ መደብ ዲሞክራሲ አይጠየቅም፤ ዲሞክራሲ በገደብ፤ ዲሞክራሲ በትግላችን ወዘተ የሚሉ ናቸው:: በጠቅላላው በዲሞክራሲ ጥያቄ ያላቸውን አቋም ለማጠናከር የሚያቀርቧቸው ምክንያቶችን ለመዘርዘርና በዚህም ጥያቄ ላይ ትችት ለመክፈት የጽሁፉና ዓላማ ስላልሆነ ትተነዋል:: ሆኖም በዲሞክራሲ ጥያቄ ላይ የሚያቀርቡቸው የከርከር ነጥቦች በማጠቃለል ጋስደን የቀኝ አድርባይነታቸው ለማስየት እንሞክራለን::

ያሉትን የዲሞክራሲ መብቶች በማፃነቅ ስለተገኙት ድሎች በመተረት የዲሞክራሲ መብቶች አለማስፈለጋቸውን ለማሰመን ይጥራሉ:: እኛም እንደነሱ የዲሞክራሲ ይዘት ያላቸው ድሎች እንደተገኙ አንክድም:: የተገኙትንም ድሎች እናጥላላም:: ቁም ነገሩ አድርባዮች የተገኙት ድሎች አከብረውና ለተጠማሪ የዲሞክራሲ መብቶች ይታገላሉ ወይ? የሚለው ነው:: ድሎችንም አያከብሩም፤ለዲሞክራሲ መብቶችም አይታገሉም:: አለማከበራቸውን እስከዛሬ ድረስ በዲሞክራሲ ሃይሎችና በህዝብ ድርጅቶች ላይ የወሰዷቸውና ያስወሰዷቸው አድሃሪ እርምጃዎች በቂ ማረጋገጫዎች ናቸው:: የዲሞክራሲ መብት መጻረራቸውንና ላለው ''ዲሞክራሲ መብት'' መስገዳቸውን የማያውቅ ኢትዮጵያዊ አለ ለማለት ያስቸግራል::

በመጀመሪያ ሪፍርሞች የትግል ውጤቶችም ቢሆኑ ማንኛውንም ዓይነት መብቶች የገዥው መደብ አይለቅም:: መብቶች [ሪፍርሞች] እንዴ ተለቀዋልና አይቀለበሱም



ማለትም አይቻልም:: የገዥ መደብ አንዳንድ መብቶች ሪፍርምስ ፕሳንቶን የሚፀረፉና የሚያስጉት ሆነው ካገኛቸው ወይ ሳለመልቀቅ ይሞክራል ወይም ይቀለብሳቸዋል:: ዛሬ በኢትም ውስጥ ቢሆን ደርግ እንዲህ ተናካሽ ውሻ ሆኖ ለዲሞክራሲ የሚታገሉትን ሁሉ የሚበጥቀውና የተገኙትም የህዝብ ድሎች እየቀለበሰ ያለው ሌላ ትርጉም የለውም:: የቀኝ አድርባዮችም ወዝና ማሌሪድ ሚሊዮን ጊዜ የተገኙት ድሎች እያሉ ከፊውዳሊዝም ጋራ እያነፃፀሩ የሚተርቱት ሰፊው ህዝብ በሪፍርም በታኝ ብሎ ከደርግ ጋራ እንዲታረቅ ብቻ ነው:: ታዲያ ከካውትስኪ፤ ከበርንስታይን፤ ከኢዩሮ ኮሚዮኒስቶች፤ ከዘመኑ ሶሸል ዲሞክራቶች በምን ይለያሉ?

እነካውትስኪ የከበርቴው ዲሞክራሲ ከፊውዳሉ ዲሞክራሲ ይበልጣል እያሉ እንደነሱው ይተርቱ ነበር:: ግን ከከበርቴው ዲሞክራሲ የወዘደሩ ዲሞክራሲ እንደሚበልጥና ሰፊው ህዝብ ትግል እንዲያደርግ ለመናገር እንደነሱው ተለጉመው ነበር:: ልክ እንደነሱው ዛሬ ሰፊው ህዝብ ለተጨማሪ የዲሞክራሲ መብቶች ታግሉ ወደ ወሰኙ ድል እንዳያመራ እንደሚያደርጉት ማለት ነው:: ሽረ እምት ላይ ነው ልዩነታቸው? በግልጽ ሪፍርሚስትነታቸውን ካስዮት ከእነበርነስታይንና ተከታዮቻቸውስ ጋራ ያላቸው ልዩነት ምን ላይ ነው? የኛዎቹ በሸበረቀ የአብዮት ቃላቶች ሪፍርሚስትነታቸውን በመሸፈናቸው ነው? እነሱ በግልጽ ሪፍርሚስትነታቸውን በመግለጻቸው ነው? የኛዎቹ እስከአሁን የተገኙትን የዲሞክራሲ መብቶች ብቻ አጽንቶ ወደ ህዝባዊ ሥርዓት ልንሸጋገር እንችላለን እንደሚሉት ሁሉ እነበርነስታይንም ባለው የፖርላማ ዲሞክራሲ ተጠቅመን ወደ ሶሻሊዝም እንሸጋገራለን ነው የሚሉት? የኛዎቹም እንደነበርንስታይን የሰፊውን ህዝብ ነፃና አብዮታዊ እርምጃ ይፈራሉ! እነበርንስታይን በግልጽ እንደሚፈሩ ሁሉ የኛዎቹም የነቃን፤የተደራጀን፤የታጠቀን ህዝብ አመጽ በተግባር እንዳይመነዘር ይጥራሉ::

የኢት አድርባዮች አድርባይነታቸውን ለማስየት ያህል ከነካውትስኪ ጋራ አመሳስልናቸው እንጂ አሳወዳደርናቸውም:: አይወዳደሩም:: ካውትስኪ በአድርባይነት ከመቀጡ በፊት በወዛደሩ እንቅስቃሴ ውስጥ ብዙ ሚና ተጫውቷል:: እነሱ በዚህ አገር ጫፉም አይደርሱም:: የቀሩትም እነበርንስታይን ቢሆኑ ቢያንስ ቡርዡዋ ዲሞክራቶች ናቸው:: ወዝና ማሌሪድ ፤ ስደዱ|ደርግ እንኳን ለጥቆኞች ዲሞክራሲ ሊሞ የለዘብተኛ ከበርቴውን ያህል ዲሞክራቶች አይደሉም::

እውነተኛ ተራማጆች በተገኘው ዱል ሳይሸነገሉም ዱሉንም ሳያጥላሉ ለወሳኙ ትግል የሚያበቃቸው ሌላ ታክቲክ ይቀይሳሉ:: ታክቲካቸው የገዠን መደብ ያስቀይግል ለግል አስተባሰብ ሳይ ሳይሆን የሰፊውን ህዝብ ትግል ሲያፋጥን ይችላል በሚል አስተባሰብ ሳይ ይመሠረታል:: የነቃን፣የተደራጀን፣የታጠቀን ትግል በተገበር የሚመነዝር ታክቲክ ይሆናል:: በዛሬዋቶ ኢት ''ዲሞክራሲ ለጭቆናች ያለገደብ አሁን''በሚል መፈክር ሥር ይሰለፋሉ::

## ቢሮክራሲ

አስቀደመን እንዳሰየነው የአንዱን ህዝብ አብዮት አረጁምና አደካሚ ከሚያደርጉት መሃል አንዱ የመንግሥት ሥልጣን ጥያቄ ነው ብለናል:: በተለይ የመንግሥትን መኪና ጠብቆ የሚያራምደው ቢሮክራሲው በዚህ ጥያቄ ላይ ማእከላዊ ቦታ ይይዛል:: ከአለም ዓቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ጋራ ያለው ግኑኝነትና መተሳሰር፣በፖሊሱ በወታደሩ ፣በፍርድ ቤቱና በሥልጣን መሣሪያዎች ላይ ያለው ቁጥጥር ያለው አውቀትና የፀረ–አብዮት ልምምዱ፣መደራጀቱ ጥያቄውን ያከብደዋል::

በመጀመሪያ እንዲህ ዓይነት ቦታ የሚቀመጡት የሠለጠኑ ግለሰቦች በኢምፔሪያሊዝምና በገዢው መደብ የሰለጠኑና የተመለመሉ፣ ሳለው ሥርዓት ታማኝ አገልጋዮች ናቸው ተብለው የሚታመኑ ግለሰቦች እንጂ ማንኛውም አይደለም:: ሁለተኛ ያሉት የመጠቀና ኢኒስትቶዩሽን ሳይደመሰሱ [ከጥርው የተወረሱት] ግለሰቦችን ብቻ ለውጦ የቢሮክራሲውን ተንኮል መቋቋም አይቻልም:: 1ኛ ያሰራር ልምዱና አስተሳሰቡ በጥርው ዓይነት እስከቀጠሉ ድረስ ከላይ ''ተራማጅ''ናቸው ተብለው የሚጠሩ ግለሰቦች ስለተቀመጡበት ብቻ የቢሮክራሲውን ተንኮል ያቀዘቅዛል እንጂ አያጠፋውም:: በሃይራርኪው ውስጥ ያሉ መለስተኛ ቢሮክራቶችም የወረሷቸውን ልምዶች በቀላሉ አይረሱም:: ሊረሱም አይፈልጉም:: 2ኛ ጥንት የነበሩትን ግለሰቦች እንዲህ በጭር ጊዜ ውስጥ ቦታቸውን ሙሉ በሙሉ በተራማጅ መተካት አይቻልም:: እርገጥ መደባቸውን የሸጡ ምሁራን መኖራቸው በይከዱም ብዙ መደቡን የማይከዳው ደገሞ ስለሚበልጥ በምሁር አብዮታዊ ብቻ ቁልፍ ቦታዎችን ለማስያዝ ያዳግታል:: በዚህ



ዓይነት ሁኔታ አድሃሪ ምሁራንም ቁልፍ ቦታ የማያዘቸው ሁኔታ እየጠመረ ይመጣል:: ከዚህ የተነሳ ቢሮክራሲውን ለመምታት በነዱ አብዮት ውስጥ ያሳንዳች ማወላወል ተገቢ እርምጃዎች መወሰዱ ግዴታ ይሆናሉ:: የጥንቱ ያሰራር ዘዴ በዘመድ፣ በጉቦና በመሰሰሉት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ በጠቅላላ ባዲስ ያሰራር ዘዴ መተካት ይኖርበታል:: የህዝብ ሃይሎች ባስተዳደር ውስጥ ልምምዱ እንዲኖራቸውና ያስተዳደር እውቀታቸው እንዲዳብር በየጊዜው ባገሪቱ የፖለቲካና ያስተዳደር ህይወት ውስጥ በሚገባ መሳተፍ ይኖርባቸዋል:: በጉን ደገሞ በየጊዜው አድሃሪ የሆነ ቢሮክራቶች እያስወገዱ በአገር ወዳጆችና በተራማጆች መተካት ይቻላል::

ይህን እነጋገር ለመረዳት የሚቻለው እንደነወዘ ቢሮክራሲ ማለት ቢሮና የቢሮ ሰራተኛ ማለት ነው የሚል ተራ ለሆነ ዱፍን ገለፃ ስንነሳ አይደለም:: ቢሮክራሲ ማለት የቢሮ ሃይራርኪና የአስተሳሰቡ ዱምር መሆኑን ስንረዳ ብቻ ነው:: ሃይራርኪው በዐለቃና በታዥ፣ በገዢና በተገዢ ግኑኝነት ላይ የተመሠረተ ሲሆን አስተሳሰቡም ይህን ዓይነት ግንኙነትን ለማጠናከር እንጂ ለማጥፋት ወርቦ አይመኝም:: በጉቦ፣ በዘመድና በጠቅላላው ኮራፕሽን ያምናል:: ካሰራር ዘዴውም የተነሳ ሥራ ጉታች ይሆናል::

ስሰቢሮክራሲው አንዱ እርምጃ ወደፊት ሂደን ገለፃ ለመስጠት የሞከርነው በእውነቱ ባያስፈልግ ቀርቶ አይደለም:: "በስም ቢሮክራሲ ሁሉም አይመታም"፣ "ተራማጅም" አድሃሪም ቢሮክራሲ አለና ለይተን እናውራ የሚሉ የሪፎርሚስትም የበራዥነትም ይዘት ያላቸው ያድርባይነት መሥመር በወዝ ገምበር ቀደምነት በሌሎች ተከታይነት ከፋኛ ስለተስፋፋ ነው:: ''ተራማጅ ቢሮክራሲ በሶሻሊዝም እንኳን ቢሆን ይኖራል''፣ ''በጠቅላላው ቢሮክራሲ መጠቀም''ይቻላል ይላሉ::

በበኩላችን በነኚህ ተራ የአድርባዮች ቲዎሪ ላይ ጉልበትና ጊዜ አግኝተን ትችት ከማድረግ የምንቆጠብ አይመስለንም:: ለጊዜው ግን በጭሩም ቢሆን ባደ ቲዎሪዎች መሆናቸውን እናስያለን::

ከላይ ስለቢሮክራሲ የሰጠነውን ገለፃ ልብ ብሎ ያላነበበ ሰው ካልሆነ ወይም በገለፃው ጠቅላላ ይዘት ያልተስማማ ካልሆነ በስተቀር ቢሮክራሲ ከኮሚዩኒስት ህብረተሰብ በፊት አይጠፋም ብሎ አይከራከርም:: ወይም ተራማጅ ቢሮክራሲ ምንም ጊዜ ይኖራልና በደፈናው ቢሮክራሲው ይውደም ማለት አድሃሪ ነው ብሎ አፉን ሞልቶ

አይናገርም፡፡ እኛ ብንሆን ሌኒን የነኸሁን ሰዎች ተራ ቲዎሪ ዋጋ ቢያሳጣ አነ
ዲህ ይላል፡፡ ''በሩሲያ የቢሮክራሲው መኪና ሙሉ በሙሉ ተሰብሮ ትቢያ ለብሷ
ል፡፡ የአሮጌው ዳኞች [ፖኪነገ] ያደርጋሉ፤ የከበርቴው ፓርላማ ጠፍቷል፡፡
ለወዛደርና ለገበሬዎች ከፓርላማው የሚበልጥ የውክልና መድረክ ተከፍቶላቸዋል፡፡
የቢሮክራቶችን ቦታ ሶቪየቶቻቸው ወሰዱ፡፡ ወይም ሶቪየቶቻቸው ቢሮክራሲውን በቁ
ጥጥራቸው ሥር አዋሉት፡፡ ሶቪየቶቻቸው ዳኞቻቸውን የመምረጥ መብት ተሰጣቸው..."
ቅ 3 ገጽ 85—86

ቢሮክራሲው የተመሠረተው ለኢምፔሪያሊዝምና ለተከታዮቹ አገልጋይ እንዲሆን
ነው፡፡ ቁልፍ ቦታዎችም የሚይዘው ያገለግላሉ ተብለው በሚታመኑ ብቻ ነው፡፡
ከዚህ የተነሳ ተራማጆች በቁልፍ ቦታዎች ላይ ለመቀመጥ ያላቸው እድል የመነመነ
ነው፡፡ አልፎ አልፎ እንደ ጠብታ ተራማጆችና አገር ወዳዶች ከፍተኛ ቦታ ይዘው
ቢገኙም በጠቅላላው ኢንስቲትዩሽኖች ላይ የሚያመጡት ውጤት አይኖርም፡፡ አብዮታ
ዊ መንግሥት ከተመሠረተ ተራማጆች ቁልፍ ቦታዎች ላይ የመሾም እድል ያጋጥማቸዋ
ል፡፡ ነገ የጥርውን ያሠራር ዘዴ ጠርሶ ካልጠፉና የነበሩት ኢንስቲትዩሽኖች
ካልተለወጡ ዘር ዘር የሚጠናከረው ቢሮክራሲያዊ ያሰራር ዘዴና ቢሮክራሲ ነው፡፡
ከዚህም የተነሳ የተራማጅ ግለሰቦች በቁልፍ ቦታ መቀመጥ ጥሩ ቢሆንም በቂ ነው
ማለት አይቻልም፡፡ የህዝብ ሃይሎች በአስተዳደር ውስጥ መሰማራትና የጥንቱን ያሠ
ራር ዘዴ በዲስ መተካት ያስፈልጋል፡፡ ቀጥተኛ የህዝብ ተሳትፎ መጠመር አለበ
ት፡፡ ይህ ተሳትፎ ብዙ የቆይ አጥቂዎችን[ሬድ ኤክስፐርትስ] ከወዛደሩ ውስጥ
እንዲወጣ ያደርጋል፡፡ እውቀት የጥቂቶች ሞኖፖል መሆኑ ቀርቶ የብዙሃኑ ይሆናል
ማለት ነው፡፡ በመሪዎችና በተመሪዎች መካከል ያለው ግኑኝነት በዐለቃና በጭፍራ
በጌታና በተገዥ መካከል ሳይሆን በጓዳዊ [ኮመሬድሽፕ ሪለሽን] ግንኙነት ላይ
ይመሠረታል፡፡ ይኼ ዓይነቱ የህዝብ አስተዳደርና ተሳትፎ ጉቦ ዝምድናን ኮራፕሽ
ንን ያጠፋል፡፡ ሁሉም በይፋ ነውና፡፡ ብዙዎች ነገሮች በሰራው ህዝብ ሊፈቱ
ስለሚችሉ ዲሬክተሩን ሚኒስትሩን ገዝውን በመጠበቅ ጊዜያች አይባከኑም፡፡ እውነ
ተኛ ሶሺያሊዝምን የመሠረተ አገር ወይም ወደ ሶሺያሊዝም የሚያመሩ አገሮች የሚይ
ዙት አስተዳደር ይህን ይመስላል፡፡ ነገ በሶሺያሊዝም ሥም የሚመጻደቁ በሪቪዥኞችና
ሪፎርሚስቶች የሚኖራቸው አስተዳደር ቢሮክራሲያዊ ነው፡፡ ''ተራማጅ ቢሮክራሲያ
ዊ'' የአሠራር ዘዴን ይመርጣሉ፡፡ የሰራው ህዝብ ተሳትፎ የሞላበትን አስተዳደር
ሳይሆን ጥቂቶች የፖርቲው አባላት የሆኑ ''ተራማጅ ቢሮክራቶች'' የሚመሩትን አስ
ተዳደር ያስበልጣሉ፡፡ የነወዝ ዱንፋታም ከዚህ አያልፍም፡፡ ዘሬ በዚህ ጥያቄ



ላይ ተራማጅ ቢሮክራሲ አይመታም የሚባለው ፈሊጥ የእውነተኛውን የህዝብ አስተዳደ
ርና ሶሻሊዝም ከመፍራት የሚመነጭ የቀኝ አድርባዮች የሪፎርሚስትና የሪቪዥኒስት
ቲዎሪ ነው፡፡

## <u>በ ብ ሔ ር ጥ ያ ቄ ላ ይ</u>

በብሔር ጥያቄ ላይ የቀኝ አድርባዮች ትምክህተኝነት ያጠቃቸዋል፡፡ በም
ንም ጊዜና የታሪክ ሁኔታ ቢሆን የብሔሮችን እስከመገንጠል ድረስ ያላቸውን መብት
አይቀበሉም፡፡ በዚህ ደረጃ ያላቸው አቋም ከአውቶኖሚና ከፌዴሬሽን አያልፍም፡፡
የመገንጠልንም መብት ጨምሮ ማወቅን አይነተኛ ከሚያደርጉት መሃል ሁለት መሠረታዊ
ምክንያቶች እንጥቀስ፡፡ 1ኛ የብሔሮች አንድነት በመፈቃቀርና በእኩልነት ላይ
መመሥረት ስለሚገባው፡፡

2ኛ ከመደብ ትግል አንፃር ለአንድነቱ ብቻ ሳይሆን ለመገንጠሉም መብት
አጅቴት ማድረግ የሚያቀጣበት ጊዜ ስለሚኖር ነው፡፡ ለምሳሌ በተጨቆኑ ብሔሮች
መሃል ጠቅላላው አብዮታዊ ሁኔታ አመች ሆኖ ይገኛል፡፡ በጨቋኙ ብሔር ውስጥ
ፀረ—አብዮት ሁኔታ ይኖራል፡፡ በዚህን ዓይነት ሁኔታ ውስጥ የመገንጠሉ ጥያቄ
ከጨቋኙ ብሔር የመጣውን ገዥ መደብ የሚዳከምበትንና ለጠቅላላው አብዮት አመችን
ሁኔታ ሊፈጠር የሚችልበትን መንገድ ይከፍታል፡፡ ይህን ጠቅላላ ፕሪንሲፕል በመ
ከተል ተራማጆች በብሔሮች ላይ ያላቸው አቋም እስከመገንጠልም ጭምር እንዲሆን በ
ፕሮግራማቸውና በልሳኖቻቸው አማካኝነት በግልጽ ያሳውቃሉ፡፡ እንደ አድርባዮች
በአውቶኖሚና በፌዴሬሽን አይገቱትም፡፡ የቀኝ አድርባዮች በብሔሮች ላይ ያላቸው
ን አቋም እስከገቶት ድረስ ከላይ እንዳሳየነው ለመገንጠሉ ጥያቄ በጠቀስነው መል
ክ አጅቴት ማድረግ የሚያስፈልገበት ሁኔታ ቢፈጠር እንኳን አጅቴት አያደርጉም፡፡
እንዲውም ከየብሔራቸው ከበርቴና ንዑስ ከበርቴ ጋራ ሆነው ለጭፍን አንድነት ይታ
ገላሉ፡፡ አድርባዮች በአንደኛው ዓለም ጦርነት ጊዜ እንዳሳዩት ርካሽነት እነሱ
ም የየአገራቸውን ጭቁን ህዝብ በሌሎች ብሔር ጭቁን ህዝቦች ላይ እንዲነሳ ቅስቀ
ሳ ያደርጋሉ፡፡ በመጨረሻም ትምክህተኝነት ወደ ግልጽ ፀረ—አብዮተኝነት ተለውጦ
የፀረ—አብዮት ሃይልን በአብዮት ላይ ያዘምታል፡፡

ከላይ የመገንጠልንም መብት ማወቅ ያስፈልጋል በምንልበት ጊዜ አንድነት ለእኩልነትና በመፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ መሆን ስለሚገባው ነው ማለታችን ይታወሳል:: እኩልነትና መፈቃቀድ ከጠፉ አንድነት እውነተኛ አንድነት ሳይሆን በሃይል ወደተገነባ ሰው ሰራሽ አንድነት ያመራል:: ይህ ዐይነቱ አንድነት ደግሞ ህዝቡን ጠብቆ መፍረክረኩ አሌ የማይባል ሃቅ ነው:: ለምሳሌ የሴትዮይቱን የመፋታት መብት ህጉ የሚያውቅላት ከሆነ የባሏ ተገዢ መሆኗ ይቀራል:: ይህ ማለት ግን አብረው እንዳይኖሩ ጥሪ ማቅረብ ማለት ሳይሆን፣ አብረው ለመኖር የማይችሉበት ሁኔታ ከተፈጠረ ሴትዮይቱ የባሏ ተገዥ ሆና እንዳትኖር የመፋታት መብቷን ታውቃለች ማለት ነው:: እንግዲህ የብሔሮቻችንም እኩልነት ሆነ የጋብቻውንም ምሳሌ በሚመለከተው በኩል የመገንጠሉና የመፋታት መብቱን ጭምር አለማወቅ ተፈቃቅደ መኖር የማይቻልበት ሁኔታ ቢፈጠር እንኳን ምን ተደርጎ ትለያያላችሁ ማለት ነው:: አለመፈቃቀዱ ሺህ የማያስፈልግ ደም መፋሰስና ሺህ ጥላቻ ቢያስከትል ሚልዮን ጥቆናን ቢያመጣ ፍንክች አለማለት ነው:: ግልጽ ትምክህተኝነት ግልጽ ግን አህሎኝነት ይለዋል ይህ ነው::

ዛሬ በኢት ውስጥ ያሉ የቀኝ አድርባዮች ወዝና ማሌሪድ በብሔር ጥያቄ ያላቸው አቋም ውስን ነው:: ከገዥው መደብ በተለይም ከደርግ/ሰደድ ቅንጣት አይለዩም:: ፕሮግራሞቻቸውም ሆኑ ልሳኖቻቸው በግልጽ የሚያሳዩን ነገር ነው:: እነኚህ አድርባዮች ይህን አቋማቸውን ለማጠናከር ብዙ ምክንያቶች ይደረድራሉ:: ሁሉም ግን ከማርክሲዝም ሌኒኒዝም መሠረታዊ ፕሪንሰፕሎች ጋራ ምንም ዓይነት ዝምድና የሌላቸው ምክንያቶች ናቸው:: ሸረ ለመሆኑ አንድ ትምክህተኛ የሆነ አስተሳሰብ ከማርክሲዝም ሌኒኒዝም ጋራ እንዴት ይዛመዳል? የመገንጠል መብት ጭምር ማወቁ አጠቃላይ የሆነ የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ፕሪንሲፕል ነው:: ለመገንጠል አጅቴት ማድረጉ በመጠኑም ቢሆን ከላይ እንዳሳየነው በተወሰነ የታሪክ ወቅት ውስጥ የሚወሰድ አቋም ነው:: ህያው የሆነው የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ፕሪንሲፕል ይኼ ከሆነ ወዝና ማሌሪድ አጠቃላዩን የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ሰርዘው ከፕሮግራማቸው ውስጥ የመገንጠል መብት ያሳወቁት ለምን ነው? እነሱ እንደሚሉት ዛሬ የኢ ወ አ ደርግ አብዮታዊ በመሆኑና የተቀሩት የብሔረሰብ ንቅናቄዎች በተለይም የኤርትራ ጥያቄ አድሃሪ በመሆኑ ነው? እነሱ እንደሚሉት የኢ ወ አ ደርግ አብዮታዊ ቢሆን የተቀሩትም የብሔረሰብ ንቅናቄዎች አድሃሪዎች ቢሆኑም እንኳን የመገንጠልን ጥያቄ በአጠቃላይ ፕሪንሰፕሉ ከመቀበል የሚያግድ ነገር ፈጽሞ አይኖርም:: ስለነኚህ አድርባዮች አንድ ጥያቄ እናቀርብላቸዋለን:: ዛሬ እነሱ አብዮታዊ የሚሉት ደርግ



ነገ ቢገለበጥና ፀረ—አብዮት ቢሆን ወይም በሌላ ፀረ—አብዮት ሃይል ቢተካስ? በዛው መጠን በጭቁን ብሔረሰቦች ውስጥ ያለው አብዮታዊ ሁኔታ ቢፋፋምና የፀረ—አብዮትን ሁኔታን ለማዳከም በመገንጠል ጥያቄ ላይ አጅቴት ማድረጉ የሚያስፈልግበት ሁኔታ ቢፈጠርስ? አድርባዮች ምን ያደርጋሉ? ፕሮግራማቸውን አሻሽለው የመገንጠልን መብት ይጨምራሉ? ነው ወይስ ይኼ የተባለው የሁኔታ መለዋወጥ ሳይከተል ሁሉም ነገር አሁን አለ እንደሚሉት ያዘግማል ይላሉ::

ለማወናበድ ካልሆነ በስተቀር ፕሮግራማቸውን አይቀይሩም:: ምክንያቱስ? ምክንያቱማ የመገንጠልንም መብት ጭምር ቢያንስ በፕሮግራም ደረጃ ያንድን ብሔር መብት ማወቅ አጠቃላይ የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ፕሪንሰፕል ነው:: ይህን አጠቃላይ ፕሪንሰፕል አስቀድሞ በፕሮግራም አማካኝነት ማወቅ የማንም ማርክሲስት ሌኒኒስት አቋም ነው:: አያውቁትም ለማለት ሳይሆን ሊቀበሉትም አልፈለጉም:: ሁኔታውም ምንጊዜ ሊለዋወጥ እንደሚችል ያውቃሉ :: ግን ያው የትምክህተኝነት አቋማቸው አያነቃቸው የመገንጠልን መብት እንዳይጨምሩ አድርጓቸዋል:: ነገርን የሚያዩትና የሚለኩት ከወዛደሩ የመደብ ትግል አንፃር ሳይሆን ከራሳቸውና ከየብሔረሰባቸው ከበርቴ ጥቅም አንፃር በመሆኑ ያልነው የሁኔታ መለዋወጥ ሊመጣ መቻሉ ብዙም አያሳስባቸውም:: ምክንያቱም አሁን የሚሉት የደርግ አብዮታዊነት ቢያከትምም ወይም በፀረ—አብዮት ቢተካም የያዙት አቋም ለየብሔረሰባቸው ከበርቴ ተስማሚ እንደሆነ ይቆያል:: ከዚህ አንፃር አቋማቸው ሎጂክ አለው:: ግን በወዛደሩ ሥም እየተመጻደቁ አያወናብዱ:: ወዛደሩ የመገንጠልን መብት ጭምር የሚያውቀው አንዱም ምክንያት ነገርን ከወዛደሩ የመደብ ትግል አንፃር በመመልከቱ ነው:: ለራሱ ብሔረሰብ ከበርቴ ምንም ደንታ ስለሌለው ነው:: ወዛደሩ ሁልጊዜ አቋሙን የሚመለከተው ለመደቦች ትግል አመቺ መሆኑን ብቻ ነው::

የብሔረሰቦችን ሙሉ የእኩልነት መብት አለማወቅ ወይም በገደብ ማወቅ ዞሮ ዞሮ ከትምክህተኝነት አይወጣም:: ትምክህተኝነት እስካለ ድረስ ደግሞ ከከበርቴውና ከንዑስ ከበርቴው ጋራ መሰለፍ የማይቀር ነገር ይሆናል:: የወዛደሩን ዐላማ መሸጥ ይመጣል::

ትምክህተኝነት ደረጃ በደረጃ እራሱን በይበልጥ እየገለጸ የሚሄድ ነገር ነው:: ትላንት የነወዝና ማሌሪድ ትምክህተኝነት በፕሮግራምና በወረቀት ብቻ የተወሰነ ነበር:: ዛሬ ግን አንድ እርምጃ ወደፊት ሄዶ በደቡብ ገበሬዎች ላይ

በተግባር እየተመነዘረ ነው፡፡ ነገ ደግሞ ምን አይነት መልክ እንደሚይዝ ለመተን
በይ ጠንቋይ መቀለብ አያሻም፡፡ ከአንደኛው አለም ጦርነት በፊት ትምክህተኝነት
እስከዚህም ጎልቶ አልታየም ነበር፡፡ ጦርነቱ መፈንዳቱ የማይቀር መሆኑን የአውሮ
ፓ አድርባዮች እንደተገነዘቡ ከሰማይና ከምድር መሃል ያሉ ምክንያቶችን እየሰበሰቡ
ጦርነቱን በመደገፍ ቆሙ፡፡ የየአገራቸውን ከበርቴ ከየአገራቸውና ከሌላው አገር
ወዛደር አስበለጡ፡፡ ከአንደኛው ዓለም ጦርነት ከዛም በኋላ በየጊዜው ከታዩት ክ
ሬይሲስቶች የተገኘው ትምህርት በቀውጢ ዘመን አድርባይነት በጠቃላይ፣ ትምክህተኝነት
በተናጠል አገጠው ሊታዩ መቻላቸውን ነው፡፡

## አድርባይነት በቀውጢና በሰላም ዘመን

የቀኝ አድርባዮች በሰላሙ ዘመን ከከበርቴው ጋራ ያላቸውን ዝምድና በገሃዱ
ለማሳየት አይደፍሩም፡፡ ብዙውን ጊዜ በወዛደሩና በሰፊው ህዝብ ጭቆን ስም ስለሚ
ምሉና ስለሚመጻደቁ እንዲያውም ከከበርቴው ይልቅ የሰፊው ህዝብ ወዳጅ ሆነው የታዩ
ይመስላቸዋል፡፡

በዚህ አስመሳይነታቸው ላይ የከበርቴው የማቴሪያል እርዳታ ብዙውን ጊዜ
ስለማይለያቸው እስከተወሰነ ደረጃም ቢሆን መልካቸውን ሸፍነው ሊኖሩ ይችላሉ፡፡

የቀኝ አድርባዮች ሽፋናቸውን ተገፈው እርቃነ ሥጋቸውን የሚቀሩት በተለይ
በቀውጢ ዘመን ነው፡፡ የሚቀይሷቸው ታክቲኮች በሙሉ በሰፊው ህዝብ ጥቅም ላይ
ያልተመሠረቱ በመሆናቸው ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ጋራ አልጣጣም ብለው በገሃዱ ሲጋጩ
ይታያል፡፡ እዚህ ላይ የአድርባዮች ታክቲክ ''በሰላሙ'' ጊዜ ትክክል ይሆናል፡፡
በቀውጢ ጊዜ ብቻ ስህተተኛ ይሆናል ለማለት አይደለም፡፡ የቀውጢ ዘመን ያሉትን
የፖለቲካ ቅራኔዎች ስለሚያፋፍም የተለያዩን ታክቲኮች ለመፈተሽና ምንነታቸውን ገል
ጽ አድርጉ ለማውጣት ይረዳል፡፡ በየጊዜው እየዳበሩና እየፈለቁ ለሚወጡ የፖለቲካ
ጥያቄዎች አጣዳፊ መልሶችን ይጠይቃል፡፡ እነኚህ መልሶች ደግሞ እየዳበረና እየጠመ
ረ በሚመጣው ሁኔታ ጋራ ስለሚጋፈጡ ወዲያው ምንነታቸው ሊታወቅ ይችላል፡፡

በሩሲያ አብዮት ውስጥ ይህ አይነቱ ሁኔታ በ1905 ዓ ም ቁጣው በፈረሰበ
ት ጊዜ በገልጽ ታይቷል፡፡ በዚህ ዘመን አካባቢ የነሌኒን ፓርቲ አመራሩ በቀኝ
አድርባዮች የተቀጠ ነበር፡፡ ከቁጣው መወገድ በፊት አመራሩን በሚወክሉ አድርባ



ዮችና በነሌኒን መሃል ''የቀዘቀዘ'' ትግል ይደረግ ነበር፡፡ የሁለቱን መስመሮች
ታክቲክ በሚመለከተው በኩል የነበረው የፖለቲካ ሁኔታ ከዚህ ''የቀዘቀዘ'' ትግል
አልፎ አጣዳፊነት አስፈላጊ የሆነ ውሳኔ ላይ እንዲደረስበት አልፈቀደም ነበር፡፡
ነገር ገን የቁጣው መፍረስ በሩሲያ አብዮት ውስጥ ታላቅ የፖለቲካ ክሪዝን አስከተ
ለ፡፡ የፖለቲካ ቅራኔዎችን አፋፋመ፡፡ አጣዳፊ መልስ የሚጠይቅ ጥያቄ በየጊዜው
ይፈልቅ ጀመር፡፡ የጥያቄዎች መፍለቅና ለጥያቄዎች መልስ መስጠት ብቻ ሳይሆን የ
መልሶችም ስህተተኛነት፣ ትክክለኛነት በገሃዱ እየደጋገመ መታየት ጀመረ፡፡ የዚህን
ጊዜ የፓርቲው ሴንትራል ኮሚቴ ሸቀጠኛ ነጋዴ ይመስል እቃውን እንደሁኔታው ይለዋ
ውጣል፡፡ የጠቀሳሳውን ትግል በሚመለከተው ዋና ጥያቄ ላይ ያቀርቡት የነበረው
መፈክር ያው ቁጣው ተመልሶ እንዲመጣ ብቻ ነበር፡፡ በየጊዜው ስሉጋናችንን አሸሽ
ለናል ይበሉ እንጂ ዘረው ዘርው ቁጣው እንዲመለስና የሰፊው ህዝብ እምነቱን በቁጣ
ው ላይ እንዲጥል ከመጣር አልቦዘኑም፡፡

ወዛደሩ በቁጣው ላይ እምነት አጥቶ የአመጽ ትግሉን ያፋፋመበትና ለህዝባዊ
ሸንጎ (Consti. Assembly) የሚታገልበት ዘመን ነበር፡፡ ይህን የአመጽ ትግ
ል በሰላማዊ የትግል ዘዴ[በጠቀሳሳ የሥራ ማቆም አድማ ብቻ]ሊወስኑት ሞከሩ፡፡
ወዳጅና ጠላትን ለይቶ በሚገባ በቆራጥነት በመታገል ፈንታ በዘመኑ ከነበሩት የለየ
ላቸው ቀኞች[ካዴቶች]ጋራ አብሮ ለመሰለፍ ''የሚያቃጥል ፍላጎት'' እንዳላቸው
ገለጹ፡፡ በነገራችን ላይ ይሄ ሴንትራል ኮሚቴው ከሌሎች አብዮታዊ ድርጅቶች ጋራ
ሆኖ ከዐመጽ ትግል ማኒፌስቶ ፈርሟል፡፡ የነበረው የሃይል አሰላለፍ ስላስገደደው
ነው እንጂ ከልቡ የማይደግፈው ነገር እንደነበር በተደጋጋሚ ታይቷል፡፡ በአንደኛ
ው የዓለም ጦርነት ላይም በአውሮፓ ሶሸል ዲሞክራቶች ላይ ይሄው[ውንብድና]ታይቷ
ል፡፡ ጦርነቱ ከመጀመሩ ሁለት ዓመት በፊት ያደረጉትን ትንተና የወሰዱትን ፀረ—
ኢምፔሪያሊስት ጦርነት አቋም ከሁለት ዓመት በኋላ ሽረውታል፡፡ የጦርነቱን ትክክ
ለኛ ባህርይ ስተው በጭፍኑ ''ለአገሬ''ብለው ከከበርቴው ጋራ ተሰለፉ፡፡ ጦርነ
ቱና የወዛደሩ አብዮት የተያያዙ ስለሆነ በጦርነቱ ወዛደሩ ሊጠቀምበት ይችላል ብለ
ው አስቀድመው የተስማሙበት ሰረዙ፡፡ እንዲያውም በኢምፔሪያሊስቶች ቁጥጥር ሥር
ያለው ወታደሩ የውጊያ ሞራሉ ከፍ እንዲል መጣር አለብን፡፡ ከነአካቴው በከረንስ
ኪ ሥር ያለውን ወታደር ለመከፋፈል የሚጥሩትን ቦልሸቪኮችን እናወግዛለን በማለት
በገሃዱ የወዛደሩን ትግል ሸጡ፡፡ በፕሮፓጋንዳ ለአለም ወዛደር አብዮት ድርሻዮን
ከፍ ለማድረግ እውነተኛው ሰላም እንዲመጣ እንደቦልሸቪኮች መታገል አለብን በጭራሽ
አላሉም፡፡ አድርባይነት በቀውጢ ጊዜ እንዴት እርቃኑን እስከሚቀር ድረስ እ
ንደሚጋለጥ ለማየት ለጊዜው በነዚህ ሁለት የታሪክ ምሳሌዎች እናብቃና ለምን እስከ

ዚህ ዱረስ ተጋለጡ? ለሚለው ማአከሳዊ ጥያቄ በዱጋሚ መልሱን ሰጥተን እንለፍ:: በቀውጪ ጊዜ ብዙና አጣዳፊ ጥያቄዎች ይፈልቃሉ:: የጥያቄዎችን መልሶች ከለው ተጨባጭ ሁኔታ ላይ በመፈጠጣቸው በተግባር ይፈተሻሉ:: ባናት ባናት እየጨመረና እያደገ የሚመጣው ሁኔታ አስቀድመው የተፈተኙትን መልሶች ትክክለኛነት ወይም ስህተኛነት በይበልጥ ያረጋግጣል:: ለአዳዲስ መልሶችም አዳዲስ የተግባር ፈተና ያቀርባል:: እንገዲህ በእንዲህ አይነት የፖለቲካ ሁኔታ ውስጥ እውነተኛውን የወዛደርና የሰፊው ህዝብ ጥቅምና ፍላጎት የማያንፀባርቅ ታክቲክ ምን ብሎ ሊወጣው ይችላል? በዳተኛነት የሚንትተውም ሆነ አውቆ የሚያደፍጠው አድርባይ እስከ ስንት ጊዜ ዱምጹን አጥፍቶ እየተንተተ ሊኖር ይችላል? ገልጽ ይመስለናል:: በማንኛውም በኩል መፈናፈኛ ጠፍቷል:: አድርባዮች የቀውጪ ዘመን የበለጠ ያጋልጣቸዋል ሲባል የዚህ የመፈናፈኛው መዱረክ የመጥበብ ውጤት ነው::

በኢትም ውስጥ ወዝና ማሌሪድ[የኛዎቹ አድርባዮች]የሚቻላቸውን ያህል እንደአቅሚቲ ተመሳሰይ የአድርባይ ጠዋታ ተጫውተዋል:: ጥያቄዎችን የሚሸኩበት፣ ተንታችነት የሚያስጭበት ጊዜ ጥቂት አይደለም:: ደረጣ መለያ ጠባያቸው ነው:: ትሳንት ያደረጉትን ትንተና፣ የገቡትን ቃል ኪዳን ዛሬ መልሶ ማፍረስ መለያቸው ሆኗል:: ከሰላማዊ የትግል ዘዴ በስተቀር ህገወጡ የትግል አመጽ ምን ተደርጎ ሲሞከር ይሳሉ:: የተቀናቃኞቻቸውን ሃሳብ መቀንፀልና ማጣመምን ይመርጣሉ:: ከእውነተኛ የአብዮት ወዳጆች ጋራ አብሮ ከመሰለፍ ይልቅ ከቢሮክራሲውና ከቅጥር ነፍሰ ገዳዮች ጋራ ለመስራት ''የሚያቃጥል ፍላጎት'' አላቸው:: በአብዮት ሃይሎችና ወገኖች ላይ መዝመትንና ማዘመትን ጠባይ አድርገውታል:: ፀረ—ወዝአደርና ፀረ—ሰፊ ህዝብ ለሆኑ አድርባዮች ከዚህ የበለጠ የአድርባይነት መለኪያ ጠባይ የለም:: ለምን ወዝና ማሌሪድ[በተለይ ወዝ]በአብዮት ጥያቄዎች ላይ ይንተታሉ? ጊዜው አሩቦ የያዘቻውን ጥያቄዎች እየሸኩ፣ ለጊዜውና ለሁኔታው የማያስፈልጉ ጥያቄዎችን እያነሱ ይተርታሉ? እነኚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ሚስጥረ ስሳሴ ማገላበጥ አያሻንም:: በወዛደሩ ፍላጎትና ጥቅም ላይ ያልተመሠረተ ታክቲክ በሙሉ ሺህ ጊዜ በአብዮታዊ ቃላቶች ሲሸፋፈን ቢውል ዘር ዘር መጋለጡ የማይቀር ነው እንላለን:: በተለይ የህዝብ ትግል በሚፋፋምበትና ሁኔታዎች፣ ቀራኒዎች በየሰዓቱ በሚፈልቁበትና በሚዳብሩበት ሰዓት አድርባዮች የሚኖሯቸው አማራጮች ሁለት ብቻ ይሆናሉ:: ወይ በየጊዜው አቋምን እየገለጹ መጋለጥ፣ ወይ አቋምን ደብቆ መሸወድ ብቻ ነው:: ከዚህ የተነሳ ወዝና ማሌሪድ የደፈጣና የተንታችነት ጠዋታ ቢያስጭ አይደንቀንም:: ባልተንተተቡትና በዱፍረት



አቋማቸውን በገለጹበት ጥያቄዎች ላይ ደግሞ በሙሉ መጋለጣቸው አልቀረም:: ለምሳሌ በሩሲያ አብዮት ውስጥ ህዝባዊ ትግል በተፋፋመበትና አዳዲስ ቀራኒዎች በየጊዜው በሚፈልቁበት ሰዓት ሜንሸቪኮች ከጊዜው ጋራ የሚራመዱ ታክቲክ ከመንደፍና አመራር ከመስጠት ይልቅ ሽሽትን መረጡ:: አከሌ ከአከሌ የበለጠ ይከራከራሉ፣ የከርከሩ ሉሚክ የተያያዘ ነው ወዘተ... እያሉ በማያስፈልገና ትርፍ በሆነ ነገር ላይ አተኩሩ:: ዛሬ እነ ወዝ ስለትሮትስኪዝም፣ ስለወዝአደሩ ዲሞክራሲ ወዘተ... እንደሚያወሩት ማለት ነው:: ሜንሸቪኮች ወዝአደሩ በተጨባጭ እየተናነቀና እየታገለ አያዎት ስልጣንን የሚቀዳጀው በሰው ጭንቅላት ውስጥ ቦታ ይዞ በተቀረፀ ሃይል እጅ ውስጥ ነው ብለው አይዳሊስት የሆነ ክርክር ከፈቱ:: ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ገምገማ ከማድረግ ብዙ ማይሎች ራቁ:: በኢትም የየካቲት እንቅስቃሴ መሠረታዊ ምክንያት የሆነው አንዱ የዲሞክራሲ መብቶች ጥያቄ መሆኑ ተረስቶ አያስፈልገም ተባለ:: የኢት ህዝብ አብዮት አሳማ በእውነተኛው በወዝአደር ፖርቲ አመራር ስር ለምትመሠረተው ህዝባዊት ኢት መሆኑ ተከዳ በሰደድ|ደርግ አመራር ስር ሊመሠረት ለታቀደው የንውስ ከበርቴ ቡድን መገበርከክ ተጀመረ:: ከነአከቲውም የሶሻሊስት አብዮት ጠርሸ የባህል አብዮት ሳከሂዱ አያለ ከበሮ ለሚመታው ሰደድ|ደርግ ወዝና ማሌሪድ አስከስታ ወረጆች ሆኑ::

---

ወዝና ማሌሪድ ትላንት የገቡትን ቃል ኪዳን ዛሬ ለምን አፈረሱ? ለዲሞክራሲ መብቶች መቀደቅ ስህተት በመሆኑ ነው? ወይስ ለዚህ ጥያቄ መቀደቅ ጊዜው ያለፈበት በመሆኑ ነው? በዚህ ጥያቄ ላይም ሆነ በሌሎች ጥያቄዎች ላይ ወዝና ማሌሪድ ያደረጉት መንሸራተት ከደርግ ፍላጎትና ከሰፊው ህዝብ የትግል ደረጃ ፈጽሞ ተለይቶ አይታይም:: ደርግ|ሰደድ መጠናከርና መደላደል ሲፈልግ የሰፊውም ህዝብ ትግል በአዘው መጠን ወደወሰኙ ፍልሚያ ሲያመራ የሁለቱ ነገሮች መጋጠት የማይቀር የአዱገት ህግ ሆነ:: ደርግ|ሰደድ ሃይሉን ለማጠናከርና ለማደላደል የገዱ የሰፊውን ህዝብ ትግል መከታትና የገባቸውንም ቃል ኪዳኖች ማጠፍ አስፈላጊ መስሎ በገኘው ቦታ በሙሉ የፀረ—ዲሞክራቲክና የፀረ—ህዝብ እርምጃዎችን ማጠናከር አስፈለገው:: ወዝና ማሌሪድም በዚህ የቀውጪ ሰዓት በገልጽ የሰደድን|ደርገን አቋም መቀበል ተገደዱ:: ይህ የተፈጠረው የፖለቲካ ክሪዝ አቋምችንና ታክቲኮችን ገልጽና በተግባር ታይተው የሚረጋገጡ አደረጋቸው:: የማወናበጃ መዱረኮች ጠበቡ:: ሁኔታው ከአብዮቶ ወይም ከፀረ—አብዮቶ ታክቲኮች በስተቀር ሌላ ሶስተኛ አማራጭ ከለከለ:: ወዝና ማሌሪድም በሰፊው ህዝብ ጥቅምና ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ታክቲክ ለመቀየስ ባለመቻላቸው የደርግ|ሰደድ ተቀጥያ ሆኑ::

ሾረ ለመሆኑ የሁለተኛው ኢንተርናሲዮናሉ መሪዎችና ተከታዮች አስቀድመው የተቃወሙትን ጦርነት በኋላ ሲደገፉ በሩሲያ አብዮት ላይ ካውትስኪ የነበረውን

እጇም በኋላ ''ሲያስተካክል'' የወዛደሩንም እምባገነንነት ቀስ በቀስ እየከዳና በዓለም አቀፍ ላይ እጇዎችን እየለወጠ ሲመጣ ምክንያቶች ምንድናቸው:: የኛ አድርባዮች ወዝና ማሌሪድ ባደ ምክንያቶችን እንደሚደረዱት ያህል እነኛም ከኛዎቹ የበለጠና የረቀቀ ምክንያቶችን ይደረዱ ነበር:: ሃቁ ግን የወዝአደሩን እንቅስቃሴ በመክዳት ለከበርቴው የሰለጠ ፍቅር በማሳየታቸው ነው::

ፀረነቱን በሚመለከተው በኩል ከበርቴው የበለጠ ከበዝበዛው ሲሳተፍና ሲጠናከር መቻሉን በመረዳት ወደኋላ ብሎ ሊያፈገፍግ አልፈለገም:: በመሆኑም ፀረነቱ መፈንዳቱ የማይቀር ሆነ:: የፖለቲካል ክሪዞች ተፈሩም:: ታክቲኮች ወይ የከበርቴው ወይ የወዛደሩ ታክቲኮች ሆነው ወጡ:: የሁለተኛው ኢንተርናሲዮናል መሪዎችና ተከታዮች በከበርቴው እጇም ተቀጡ! የሩሲያንም አብዮት በሚመለከተው በኩል ካውትስኪ በኋላ ብዙ የእጇም ''ማስተካከል''አድርጓል:: ለጊዜው ግን ከካውትስኪ ሸፍጦች አንዷቷን እንደ ምሳሌ በመውሰድ ከወዝና ማሌሪድ የእጇም መስተካከል ጋራ እንዴት እንደሚመሳሰል ለማሳየት እንሞክራለን::

ሶቭየቶች ሥልጣን ከመጨበጣቸው በፊት ካውትስኪ እንዲህ ይል ነበር:: ሶቭየቶችን በማድነቅ ''ፋይናንስ ካፒታልን ለመጣል የጥንቱ የወዛደር የትግል ዘዴ በቂ አይደለም''፤ ''የሶቭየቶች በሩሲያ ብቻ ሳይሆን [በዓለም ላይ] ወደፊት ብዙ የሚጫወቱት ሚና አለ''፤ ''በካፒታልና በሌበር መሃል በሚደረገው ፀረነት ላይ ሶቭየቶች ወሳኝ ጠቀታ በመላ አውሮፖ ይጫወታሉ''ወዘተ... ይል ነበር:: ይሄ ጉደኛ ሰውዬ የብእሩ ቀለም አልደረቀም፤ ሶቭየቶች ለምን ያንዱ መደብ ተቀጊ ድርጅት ከመሆን አልፈው ወደ መንግሥታዊ ድርጅት ይለወጣሉ [እስቲት ኦርጋናይዘሽን] ብሎ ጩሽት ሲጀምር፤ እንደዚ ሲያደንቃቸው የነበሩትን ሶቭየትስ የፖለቲካ ተቀናቃኝ ከመሆን አልፈው ሥልጣን ሲጨብጡ ምን ተደርጎ ሥልጣን ትጨብጣላችሁ አላቸው:: በሌበርና በካፒታል መሃል ወሳኝ ፀረነት አያስፈልገም አለ! ለአውሮፖም ለዐለም ምሳሌ ልትሆኑ አያስፈልገም አለ! ወዘተ... ብዙ ብዙ ማስረፋት ይቻላል:: ወደቀናው ነጥብ እንመለስና የሁለተኛውም ኢንተርናሲዮናል ተከታዮች ካውትስኪም ቢሆን እነዚሁም የኛዎቹ ወዝና መሌሪድ ለእጇማቸው መንሸራተትና መክዳት የሚያስተባስሯቸው የሆነ መሠረታዊ ምክንያት አንድ ነው:: ለገዥ መደብ መበለጣቸው ነው:: ምድረ አድርባይ አይደርስ መስሏት በቷት... እንደሚሉት ብዙ ነውሩና ሁኔታው ሲያፈጥጣት ጣራ ጣራ ማየት ትጀምራለች:: ወጥሮ ሲይዛት ደገሞ ትገላገልና ታርፈቀለች::



ኸረ ለመሆኑ የኛዎቹ አድርባዮች ለምን ከህገወጡ የትግል ዘዴ ጋራ አይተዋወቁም? አሁን ያለው ሁኔታ የህገ ወጥን ትግል ስለማይጠቅ ነው? አይደለም:: በህገወጡ የትግል ስልት ስለማያምኑ ብቻ ነው:: እናሳያለን:: ''በሰላም'' አብዮትን ለማራመድ በማይቻልበት ዘመን ህጋዊውን ትግል ህገወጥ ትግል ይተካዋል:: [በሰላሙም ዘመን ቢሆን የህገወጡ ትግል እንዳለ ይዘነጋል ማለት አይደለም አብሮጉን ለጉን የሚሄድ ነገር ነው] ወይም ያለው አብዮታዊ ሁኔታ ከህጋዊው ለህገወጥ ትግል የሚያመች ከሆነ ሁለተኛው ብቻ ይመረጣል:: ህጋዊ የትግል ሁኔታ እንኳን ቢኖር ማለታችን ነው:: በጠቃላይ የህገወጥ ትግል ምንም ጊዜ ሊዘነጋ የማይችል በሰላሙም ሆነ በሰላም የለሹ ዘመን እንደሰንሰለት ተያይዞ የሚሄድ የወዛደሩ የትግል ሥልት ነው:: ህጋዊ የትግል መድረክ ከተገኘ የህገወጡ ትግል ለምን እንዳለ አይቀርም? ህጋዊውስ መድረኩ ሲጠብ ለምን በህገወጡ ላይ ማተኮር ያስፈልጋል? ያልነው አይነት አብዮታዊ ሁኔታ እንኳን ቢፈጠር ለምንስ ህጋዊ መድረክ ካለ የህገወጡ የትግል ሥልት የቅድሚያ ምርጫ ይሰጠዋል? እነዚህን ጥያቄዎች በሶስት መልሶች አጠቃሉ ለማሳየት ይቻላል::

1ኛ — ወዛደሩ የህጋዊውን መድረክ የሚጠቀምበት እስከተወሰነ ደረጃ ብቻ መሆኑን ያውቀዋል:: ከተወሰነ ደረጃ በኋላ የገዥው መደብና ወዛደሩ በህጋዊ መድረኮች ካላቸው ልዩ ልዩ አስተያየቶችና አጠቃቀም የተነሳ ህጋዊ መድረኮች ይጠባሉ:: ቢልም እንዳለ የሚቋረጡበት ሁኔታ ሊፈጠር መቻሉ ነው::

2ኛ — ወዛደሩ የመጨረሻውን ዐላማውን የሚጎናጸፈው በህገወጡ አመጽ ብቻ መሆኑን ያውቃል:: ስለዚህም ለመጨረሻውና ወሳኙ ህገወጥ አመጽ በሚገባ በየጊዜው መሰናዳት ያስፈልገዋል::

3ኛ — አብዮታዊ ሁኔታ በሚፈጠርበትና ሰፊው ህዝብ በህገወጥ ትግል ላይ በማተኮር በህጋዊ መድረኮች ላይ እምነት በሚያጣበት ሰዓት በህገወጥ አመጽ ላይ መሰማራትን የቅድሚያ ቅድሚያ ይሰጠዋል:: ሰፊው ህዝብ በህጋዊ ወጥ መንገድ ድሉችን ሊጎናጸፍ መቻሉን ሁኔታው ሲያመች በተጨባጭ ማሳየትና ማረጋገጡ ያስፈልጋል:: ሰፊው ህዝብ በህገወጥ አመጽ ላይ እምነቱ ከፍ ማድረግ ያስፈልጋል::

እንግዲህ ከነዚህ ከሶስት መልሶች የምንረዳው ሃቅ ወዛደሩ የህጋዊ መድረኮችን የሚጠቀምባቸው እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ ብቻ መሆኑና ዋና ዐላማውን የሚያረጋግጠው በህገወጡ አመጽ ብቻ መሆኑን ነው:: ይህን የትግል ስልት ለመቀበል ደግሞ

ታሪክን ብቻ ማወቅ አይበቃም:: ለራስ ጥቅምና ምቾት ሳይበለጡ የገዡውን መደብ
አስቀይማለሁ ለሚል ይሉኝታ ቦታ ሳይሰጡ፣ ቆራጥ ሆኖ መገኘትን ይጠይቃል:: የገዢ
መደብን ጥሉ የወዛደሩንና የሰፊውን ህዝብ ጥቅምና ፍላጎት ለማስከበር መነሳትን ይ
ጠይቃል:: ከዚህ የተነሳ የህገወጥ የትግል ስልት ለአድርባዮች በአጓ ሆኖ ይኖራ
ል:: አድርባዮች ዛሬ የህገወጡን የትግል ስልት የሚቃወሙት ከዚህ ሃቅ ከፊሆን
ሌላ ምን ሊሆን ይችላል:: አሁንም የወዛደሩ ጥቅምና ፍላጎት ላይ ያልተመሰረተ
ታክቲክና አቋም እስከያዙ ድረስ በምንም ተአምር ፀረ ስደይ/ደርግ የሆነ ታክቲ
ክ ሊቀይሱ አይችሉም:: ሰራባቸው መበለጥና ለደርግ መንበርከክ፣ የሰፊውን ህዝ
ብ ትግል እንዲከዱ አድርጓቸዋል:: የመደብ ወንድሞቻቸው ሚንሸቪኮችም
የአውሮፓ አድርባዮች ካደረጉት ውጪ ሌላ ምንም አላደረጉም:: ለአውሮፓ አድር
ባዮች ህገወጥ ትግል በዓ ነበር:: ከህጋዊ ትግል ሌላ በህገወጥ ትግል በፍጹም
አያምኑም ነበር:: እንዲያውም የህገወጥ አመጽ አመቺ በሆነበት ሰዓትና ይህንንም
ህገወጥ አመጽ ወዛደሩ ሊጠቀምበት በሚችሉበት ሰዓት እንደ ሚንሸቪክ አይነት አድር
ባዮች ህገወጥ አመጽን አከላከሉቃል:: የ1905 ዓ ም ቦይኮትን አጥብቀው ተቃው
መዋል:: ከዛም በየጊዜው ቦልሸቪኮች በየጊዜው ሶቪየቶችን በህገወጥ መንገድ ለማ
ደራጀትና ለማስታጠቅ በሞከሩበት ሰዓት እንቅፋት ሆነዋል:: እንደ ማንኛውም አ
ድርባይ የህዝብ አመጽ ለሰላማዊና ለህጋዊ የትግል ስልት እንዲተካ ሽንጣቸውን ገተ
ረው ታገለዋል:: እርግጥ ነው ያውሮፓ አድርባዮች የኛዎቹ አድርባዮች ህገወጥ የ
ትግል ሥልትን የተቃወሙበት በግልጽ ካለመሆኑም ሌላ በተለያዩ የታሪክ ዘመን ነው::
ዛሬ በኢት ውስጥ እንደ ሶቪየቱ 1905 ሁኔታ እንደሌለ እናውቃለን:: ግን የኢ
ት አድርባዮች እንደማንኛውም አድርባይ ህጋዊ ወይም ፀረ—ህገወጥ መሆናቸውን ለማወ
ቅ የግድ በኢት የሩሲያው 1905 ሁኔታ እስኪፈጠር የምንጠብቅበት ምክንያት አይ
ኖርም:: እንደሚባለውም አሁን ያለው ሁኔታ የህገወጥ ትግልን አይጠይቅም ብለን
ማመንም አንችልም:: አስቀድመን እንደተናገር ነው አንድ የማርክሲስት ሌኒኒስት
ድርጅት በምንም ጊዜና ቦታ በህገወጥና በህጋዊ ትግል እንደሚጠቀም አስቀድሞ በፕሮ
ግራሙ ላይ ማስፈር ግዴታው ነው:: ከቅስቀሳም ሆነ ከታክቲክ አንፃር ሁኔታውን
የሚያመቻቸው ለህገወጥ አመጽ መሆኑን በተግባር ያሳያል:: ይህ ደግሞ በሚያወጣቸ
ው መፈክሮች በእለት ተለት ተግባሩ ይገለፃል:: የት ቦታ ነው ዛሬ ወዝና ማሌሪ
ዱ ስደይን/ደርግ የሚቃወሙት:: ለህገወጥ ትግል አመቺ ሁኔታ ሊፈጥር የሚችል ቅ
ስቀሳ የሚያደርጉት? የትኛው መፈክራቸው ነው ለህገወጡ አመጽ ከደርግ ቁጥጥር ው
ጪ በሆነ መንገድ ጥርጊያ መንገድ የሚከፍት? ፕሮግራማቸውስ የት ቦታ ነው ስለ
ህገወጥ ትግል የሚያወራው? እንደእውነቱ ከሆነ አንዱም የለም:: እንዳውም ሃቁ
የተገላቢጦሽ ሆኖ የሚታየው::



## ማርክሲዝም ሌኒኒዝም አለመቀበል፤ የተቀናቃኝን ሃሳብ መቆንፀልና

### ማጣመም::

አድርባዮች የተቀናቃኞቻቸውን በተለይም የማሌዎችን ሃሳብ ሲታገሉ በሃቀኛ መ
ንገድ አይደለም:: በመቆንፀል፣ ሀረጎችንና አረፍተ ነገሮችን ከይዘታቸው ውጪ
በመጥቀስ፣ ወይም ያልተባለን ነገር ተብሏል ብሉ በማቅረብ ነው:: መቼም ይሄ እ
ራሱ በራሱ ደካማነት እንደሆነ የማያጠያይቅ ነገር ነው:: ይህ ድክም ከምን መነ
ጨ? ማንኛውም ግለሰብ ሆነ ቡድን በራሱ የአስተሳሰብ ጥሬት የሚያምንና በተቀናቃ
ኙ የአስተሳሰብ ጉድለቶች የማይጠራጠር ከሆነ የራሱንና የተቀናቃኙን አስተሳሰብ በ
ግልጽና በትክክል አውጥቶ ከማፍረጥ የበለጠ የትግል አማራጭ አያገኝም:: ግን በ
ራስ የአስተሳሰብ ጥሬት ላይ መተማመን ሲጠፋ፣ ወይም የተቀናቃኙን አስተሳሰብ ለመ
በገር ሳይቻል ሲቀር፣ ወይም ሁለቱም ተጣምረው በአንድነት ሲገኙ ከላይ ያስየነው ዓይ
ነት ተራ ውንብድናና ቅጥፈት እንደ አማራጭ ይወሰዳል:: በየጊዜው በለማቋረጥ በ
ታሪክ ውስጥ የታየ የአድርባዮች አንደኛው አይነተኛ ጠባይ ነው:: አድርባዮች ት
ክክለኛ መልካቸው በገሃድ እንዳይወጣና ማንነታቸው እንዳይታወቅ ስለሚፈልጉ ለጊዜው
ም ቢሆን ይህ ዓይነት የትግል ዘዴያቸው ሊረዳቸው ይችላል:: ከነሱ አንፃር ደህ
ና አማራጭ ሆኖ ይገኛል::

አድርባዮች በመሠረቱ ከወዛደሩና ከሶሺያሊስት እንቅስቃሴ ውስጥ ፈልሰው ያፈ
ነገጡ በመሆናቸው የወዛደሩንና የሰፊው ህዝብ ቋንቋ ቋንቋቸው እንደሆነ አድርገው
ለማስመሰል ይሞክራሉ::

ነገር ግን የአድርባዮች የህዝብ ወገንነት በቃል ደረጃ ብቻ የተወሰነ በመሆ
ኑ ከተራማጆች ጋራ ክርክር በሚገጥሙበት ጊዜ ሁለቱ ወገኖች ፈጽሞ የተለያዩ ሆነው
ይታያሉ:: በማይጣጣሙ በሁለት የተለያዩ ቋንቋዎች በግራና በቀኝ መተሳሰፍ ይጀም
ራሉ:: በዚህን ጊዜ በአድርባዮች ካምፕ ውስጥ ሳይሳዩን ግልቢያ፣ ግራና ቀኝ ረ
ገጣ በገሃድ ይታያል:: እቺን ድፈጣ ለማምለጥና ከሰፊው ህዝብ ለመሸፈን ሲባል
ተንኮል በሚትር ይመተራል:: የተቀናቃኞቻቸውን ሃሳብ ማጣመም፣ ሃረጎችንና አረፍ
ተነገሮችን ከይዘታቸው ውጪ መጥቀስ፣ አሉብልታን ማሰራጨት ይፋፋማል:: በጭሩ ከ
ገሃዱ የመሥመር ትግል ሽሽት ይጀመራል:: ለማወዳደርና ለማመሳሰል የሞከርነው
ማርክሲዝምን ሌኒኒዝምን ተቀብለናል የሚሉ የቀኝ አድርባዮችንና እውነተኛ ተራማጆች
ን ነው:: እዚህ ላይ አንድ መታወቅ አለበት የምንለው ነገር አለ:: አድርባዮ
ች ከወዛደሩና ከሶሺያሊስት እንቅስቃሴ አፈንግጠው የወጡ ናቸው ስለተባለ ሁሉም

<u>በቃል ደረጃ አንኳን ቢሆን ማርክሲዝም ሌኒኒዝም</u> መመሪያችን ነው ብለው ይናገራሉ ማለት አይደለም:: ገሚሶች ተቀብለናል ሲሉ ገሚሶች ደግሞ ሌኒኒዝምን ያስወገዱና ማርክሲዝምን ብቻ ተቀብለናል ይላሉ:: እንደነሱ እኛም ማርክሲዝም ለብቻ ሌኒኒዝም ለብቻ ብለን የማይነጣጠል ሰንሰለት ለመነጣጠል ሳይሆን ሃሳባችን በአድርባዮች መንደር ውስጥ በዚህ ደረጃ ''ልዩነት''እንዳለ ለማሳየት ነው:: ለምሳሌ፣ የሁለተኛው ኢንተርናሲዮናል ተከታዮች የዘመኑ የአውሮፓ ሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲዎች እንዲሁም ኢዮሮ ኮሚዩኒስቶች ሌኒኒዝምን ገንጥለው ማርክሲዝምን ብቻ ''ተቀብለናል'' የሚሉ የቀኝ አድርባዮች ናቸው::

በኢት የሶሺያሊስት እንቅስቃሴ ውስጥ እስካሁን ድረስ ሌኒኒዝምንና ማርክሲዝምን ደፍሮ የሚነጣጥል የቀኝ አድርባይ አላየንም:: ጉልተው የምናያቸው የኛዎቹ የቀኝ አድርባዮች በሙሉ ማርክሲዝምን ሌኒኒዝምን በቃል ደረጃ ተቀብለናል ብለው የሚበርዙ [ሪቪዥኒስት] ናቸው:: የቀኝ አድርባይነት የትኛውንም መልክ ቢይዝ ሪፎርሚስት ቢሆን ሪቪዥኒስት በመሠረቱ ማርክሲዝምን ሌኒኒዝምን እንደድርጊት መመሪያው አድርጎ ለአብዮታዊ ተግባር አይገለገልበትም:: ማርክሲዝምን ሌኒኒዝምን የሚቀበለው ለገሉ ጥቅም መገልገያ እስከሆነው ድረስና ሊያወናብድበት እስከቻለ ድረስ ብቻ ነው:: ከላይ እንዳሳየነው ከተራማጆች ጋራ የሚኖራቸው የአስተያየት ልዩነት የሚመነጨው ከዚሁ መሠረታዊ ሃቅ ነው:: አድርባዮች ማርክሲዝምን ሌኒኒዝምን ለራሳቸው መገልገያ ለማድረግ በሚያደርጉት ሙከራና በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ቀጥተኛ ትርጉም መሃል ገጭት በመነሳቱ ነው::

ወደ ኢት ጊዜያዊ ሁኔታ ብናመራ የኛዎቹ አድርባዮች ማርክሲዝምን ሌኒኒዝምን በቃል እንጂ በድርጊት እንዴት እንደማይቀበሉ በመጠኑም ቢሆን ለማየት ይቻላል::

መቼም ዛሬ ሰሰስተ አድርባዮች በገልጭ ውይይት እናምናለን ፀረ—ሀሜተኞች ነን ብለው አፋቸውን ሞልተው መናገራቸው አልቀረም:: ተናገሩም አልተናገሩም ገልጽ ውይይትን እንደጦር መፍራታቸው ያደባባይ ሚስጥር ነው:: ይህ ካልሆነ በአዲስ ዘመን ላይ ተከፍቶ የነበረው የዲሞክራሲ ጥያቄ ውይይት ለምን ተዘጋ? የመኢሶን አባላትና የዲሞክራቲክ ሃይሎች ለምን በመብራት እየታደኑ ታሰሩ? ለምን ይገዳሉ? እነኚህን የመሳሰሉትን ብዙ ጥያቄዎች ማንሳት ይቻላል:: አንድ ማርክሲስት ሌኒኒስት ነኝ የሚል የፖለቲካ ቡድን ማንኛውም ሃሳብ ተታግሎ እንደሚያሸንፍ ሙሉ እምነት ስላለው ፊት ለፊት ከመጋፈጥ ወደኋላ አይልም:: ተሳስቶም ከሆነ ከስህተቱ ለመማር ዝግጁ መሆን ይገባዋል:: በእውነት ሐቀኛ ከሆነ ደግሞ ከሌሎች ሃቀኛ



የማርክሲስት ሌኒኒስቶች ጋራ የሃሳብ ልዩነት ሲኖረው ለነገሩ የተለየ ክብደት ሰጥቶ ለውይይት ክፍት መሆን ይገባዋል:: አስቀድመን እንደጠቆምነው ሳንዱ እውነተኛ ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅት ከዚህ የበለጠ ምንነቱን በህዝብ ፊት የማሳወቂያ ጥሩ አማራጭ የለም:: ዛሬ ሰደድ ወዝና ማሌሪድ ይህን አማራጭ ተቀብለዋል ከማለት በሬ ወለደ ብሎ ማውራት ይቀላል:: በራሱ ላይ የማይተማመን ተቀናቃኙን የፖለቲካ መስመር ለመበገር የማይችል ሀሰተኛ ኮሚኒስት የሚያደርገው ድርጊት ነው:: እውነተኛው ኮሚዩኒስት ተሳስቻለሁ ብሎ አይፈራም:: ከሰፊው ህዝብ ጀርባ በሚደረግ ሴራ፣ተራማጆችን በማሰርና በመግደል አያምንም:: የኛዎቹ አድርባዮች ማርክሲዝም ሌኒኒዝም የቃል እንጂ የድርጊት መመሪያቸው ካልሆነ ይኸን ፀረ—ማርክሲስት ሌኒኒስት አማራጭ ለምን ተቀበሉ?

ሀሜተኞችም አይደለንም ይሉ ይሆናል:: ይኼ መቼም ሉጂክ አይሆንም:: ተራማጆች አስረውና ገድለው በጋዜጣው እንደፈለጉ ለብቻቸው ይፈነጩበታል:: በየሴሚናሩ ላይ አየሄዱ ገለፃ ይሰጣሉ:: ሴሚናሮች እነሱ በሚፈልጉት የፖለቲካ መንገድ እንጂ በተለየ አቅጣጫ እንዲያመራ አይፈልጉም:: ከነሱ የፖለቲካ መሥመር ውጭ የሆነ ውይይት ከተካሄደ ወይም ጥያቄ ከተነሳ ''ቀኝ መንገደኛውን አስቆመው''በሚል ፈሊጥ ይጠቁናሉ:: በጭራ የነሳቸውን የፖለቲካ መስመር ለመሥማት እንጂ የሌላውን የፖለቲካ መስመር ለማዳመጥ ትእግሥት አጥተዋል:: ህዝቡም ከነሱ ቁጥጥር ውጭ እርሱ በርሱ በልዩ ልዩ ሃሳቦች ላይ እንዳይወያይ ለጉመውታል:: ታዲያ በእንደዚህ አይነቱ ሁኔታ አድርባዮች የሚያካሄዱት ውይይት ከሀሜት በስተቀር ሌላ ምን ሊሆን ይችላል? በየሴሚናሩ፣ በየጋዜጣው፣ በየቦታው እነሱው ብቻ ስለራሳቸው የፖለቲካ መስመር ካወሩ እነሱው ብቻ የሌላውን ፖለቲካ መሥመር ከተቹ ነገሩ ከገልጽ ውይይት ወደ ሃሜት ዘሯል ማለት ነው:: ገልጽ ውይይት መፍራትና ሀሜት ፀረ—ማርክሲዝም ሌኒኒዝም የሆነ የአድርባዮች ጠባይ ነው:: ማርክሲዝምን ሌኒኒዝምን ለጥቅሙ መገልገያ ለማዋል ለማይፈልግ በራቸ ሳልሆን ሃቀኛ ኮሚዩኒስት ሲያልፍም አይነካውም:: ይኼ ብቻ አይደለም በየቦታው የጠቀስናቸው የቀኝ አድርባይ ጠባዮች የሚያረጋግጡት የኛዎቹ አድርባዮች ማርክሲዝምን ሌኒኒዝም እንደሚበርዙ ነው:: በብሔር ጥያቄ ላይ በተንታችነት፣ በቢሮክራሲ፣ በደርግ፣ በዲሞክራሲ ጥያቄ ላይ በትግል ዘዴዎች፣ በአርዳታ ወዘተ... ጥያቄዎች ላይ ያሉዋቸው አቋሞች ተጨማሪ ማረጋገጫዎች ናቸው:: ውዥምብር የተሞላበትን የፖለቲካ ሁኔታ ያስከተሉ የፖለቲካ አቋሞች ናቸው::

## ውዥምብር

ዛሬ በኢት ውስጥ ያለው የፖለቲካ ሁኔታ በቲዎሪ ውዥንብር ተውጧል ማለት ይቻላል:: የአንድ አገር አብዮት የቲዎሪ ጥራት የግድ ያስፈልገዋል:: የዕድሉ ወሳኝ ነውና:: በአራት አመት ዘመን የኢትን አብዮት አጢኖ ለተመለከተ ሰው የዚህን ጥያቄ አስፈላጊነት ለመረዳት አያዳግተውም::

የዛሬን አያድርገውና ኢህአፖ በወጣቶ የትግል ፍላጎት በመጠቀም ልብ የሚሰብቅ፣ ወኔ የሚቀሰቅስ ውዥንብር የተሞላበት ፖለቲካ አስፋፋ:: እስከተወሰነም ደረጃ ቢሆን ፍላጎቶ እንደሰመረለት ያየው ነገር ነው:: ደግነቶ ኢህአፖ ፖለቲካውን ለመከላከል መከራ ሲያደርግ በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ሽፋን ስለነበር በብዙም ጥረት ቢሆን መልክ ያለው የመሥመር ትግል ለማድረግ ተቻለ:: በመጠኑም ቢሆን በመጠረቭ በተገኘው የቲዎሪ ጥራት መሰረት የኢህአፖ ውዥንብር ሊመታ ቻለ:: ከኢህአፖ ጋራ የተደረገው ትግል ዛሬ እንደቀላሉ በሁለት ዓረፍተ ነገር አንዘጋው እንጂ ብዙ ህይና ብዙ ጉልበት እንደጠረሰ የማንረሳው ነገር ነው:: እንደአውነቶ ከሆነ አሁንም ቢሆን ትግሉ መቀጠል ያለበት ነገር ነው:: ያኔም ሆነ አሁን የኢህአፖ አይነተኛ ጠበቆች ናቸው ከሚባሉት ውስጥ አንዱ ወጣቶን ለገልጽና ለዲሞክራሲያዊ ውይይት ዝግ እንደሆነ የሚያደርገው መከራው ነው:: እዚህ ላይ ኢህአፖ ውዥምብር ነዝቶ ነበር ብሎ ለመተረት ባይሆን ውዥምብሩ ማንን ጠቀመ? ማንን ጎዳ? ለምንስ ውዥምብርን ማጥራት ለምን አስፈላጊ ሆነ የሚሉትን ጥያቄዎች አንስተን ካለፈው ትምህርት እንዱንቀስም ነው:: የቲዎሪ ጥራት ባይኖር የትም ይሁን የት ተጠያቂው የፀረ—አብዮት ሃይል ነው:: ኢህአፖ ስንቶን ሃቀኛ ነው አሳስታ ያስጠረሰችው? ቤቶ ይቁጠረው:: ሃቀኛ ተራማጆችን እስከህይወም ቢሆን ለመነጠል [አይበሉት] በመቻሏ ጊዜያዊ እንቅፋት ሆነባቸው ነበር::

ያኔ ኢህአፖ በጀመረችው ዓይነት ድንፋታ ተራማጆች ቢደነግጡና ከትግሉ ገሸሽ ቢሉ፣ ወይም የኢህአፖን አይነት የትግል ዘዴ ተከትለው በቲዎሪ ጥያቄ ላይ ባያተኩሩ፣ ኢህአፖም አትጋለጥም ተራማጆችም አይጠናከሩም ነበር ብሎም የኢት አብዮት የዛሬውን አያድርገውና ወደፊት ሊገፉም ባልቻሉም ነበር:: ''ያለአብዮታዊ ቲዎሪ አብዮት እንደማይኖር''ከመጽሀፍ ብቻ ሳይሆን ከራሳችን ኤክስፐርያንስ የቀሰምነው ሃቅ ይሆናል ማለት ነው:: ሙት ወቃሾች እንሁንና ኢህአፖ ከሃቀኛ የፖለቲካ ትግል ለምን ውዥምብርን መረጠች ብለን ለመጠረቭ ጊዜ አራባችንን



እንጠይቅ? አዎ! ኢህአፖ የገራ አድርባይ ድርጅት ነው:: ሁሉንም ነገር በጭፉ ተፈጽሞ ለማየት ይፈልጋል:: ለረጅም ትግል ትእግስት የለውም:: ለተጨባጩ ሁኔታ እውር ነው:: ማርክሲዝም ሌኒኒዝም ደግሞ ከረጅም ትግል እንጂ ከአጭረኛው ጋራ ዝምድና የለውም:: ከተጨባጩ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ የድርጊት መመሪያ እንጂ ብቻውን የቆመ የወንጌል ትምህርት አይደለም:: ከዚህም የተነሳ ኢህአፖና ማርክሲዝም ሌኒኒዝም ጋራ ዝምድና ያጣል:: ግን ውዥምብር የነዛው ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅት እንደሆነ በማስመሰል ስለነበር የሃቀኛ የርእዮተ ዓለም ትግል ተደርጎ ማንነቶ እንዳይታወቅ የግድ መጣር ይኖርበታል:: ኢህአፖ ውዥምብርን ከቀጥተኛ ትግል ቢመርጥ የማያስገርመው ከዚህ የተነሳ ነው::

የዛሬውን የኢት ፖለቲካ ሁኔታ ብንመለከት ከጥቂት አመታት በፊት በኢህአፖ ''ገናናነት''ዘመን የነበረው የቲዎሪ ውዥምብር እንደገና ተመልሶ እናገኘዋለን:: ከመንገሥቶ እስከ ''ህቡዕ''ድርጅት ድረስ ያሉት ጋዜጦች ሆነ ብለው የቲዎሪ ውዥምብር ይነዛሉ:: ከጊዜያዊ የአብዮት ጥያቄዎች አልፈው እስከ ዓለም ዓቀፍ ይደርሳሉ:: ውዥምብሩ የት ያቆማል ከማለት ጥራት ያላቸው ጥያቄዎች የት ይጀምራሉ ብሎ ማለቶ ይቀላል:: የ''እናት አገር ጥሪ''ትክክለኛ አብዮታዊ ይዘቶን ስቶ የደርግ ቀኝና የቢሮክራሲው መጠናከሪያ ሆኖ እንዲያገለግል ተደርጓል:: ዛሬ በኢት ውስጥ ይህ መፈክር የመደብ ትግሉ ሌላኛው ገጽ መሆን እንዳለበት የቢሮክራሲውና የደርግን ቀኝ ክንፍ ማዳከሚያ፣ የሰፊውን ህዝብ ትግል ማጠናከሪያ መሆን እንደሚገባው የሚያስቡ ቲዎሪያች አሉ ለማለት ያዳግታል:: ቢኖርም የጥይት ቀለብና የወህኒ ቤት መኖ እየሆኑ ናቸው::

ቀይ ሽብር እንዳለ ትርጉሙን ስቷል ቢባል ከሀቅ አይርቅም:: ጠበንጃ ቀርቶ ዱላ ያልያዙ ኮሚዩኒስቶችና አገር ወዳዶች በቀይ ሽብር ስም ነጭ ሽብር እየተካሄደባቸው ነው:: ዛሬ አድርባዮች ከደርግ ቀኝ ክንፍና ከቢሮክራሲው ጋራ የሚያደርጉትን ፀረ—ኮሚዩኒስት ዘመቻ ''ቀይ ሽብር''በሚል ስም ከርስትና አንስተውታል::

ቢሮክራሲው የቢሮ ሃይራርኪ መሆኑ ይሸወድና መመታት የማይቻል ነገር ነው ይባላል:: የሃይራርኪውና የአስተሳሰቡ [ፍልስፍናው] መኖር እንደሆነ ቢሮክራሲ የሚያስገኘው ጠርቦ ይዘነጋና በተራ ጥራዝ ነጠቅ ቲዎሪ ይተካል:: ቢሮክራሲ የቢሮ ሰራተኛ ማለት ነው ተብሎ ይለፈፋል::

የፍኩይዝም አራማጁና መሪ የሆነው ቼጉቬራ እንደ አብዮት መሪና መምህር ተቆጥሮ ስለሱ በየጋዜጣው ይተረካል:: ለነቃ፣ለተደራጀና ለታጠቀ የህዝብ አመጽ ወደጎንም ጠባንም ጣውንት ነው ቺናሱ የተነቀፈን ፍኩይዝምን ማስፋፋት የሰራውን ህዝብ አብዮታዊ ተሰትፍ ማጨናገፍ ማለት ነው::

በኤርትራ ጥያቄም ላይ በኢት ህዝብ ጭንቅላት ላይ ለመትከል የሚሞከረው ኤርትራ ወሰኝ የሰራው ህዝብ ትግል አጋዥ እንደሆነ አድርጉ በማቅረብ ነው::

የውጭ ኤርትራ ባይገኝ የኢት ካርታ ሊለወጥ ይችል እንደነበር ሲያወሩ ኤርትራውን ተከትሉ የመጣውን የቢሮክራሲውንና የደርገን ቀኝ ክንፍ መጠናከር "የብሄራዊ ነፃነት"መደፈርን ጉዳይ ቃልም አይተነፍሱም:: በዚህ ጥያቄ ላይ ትክክለኛና ሃቀኛ ውይይት ሲከፍቱባቸው ፖፖሊስት በሆነ መንገድ ነገሩን ለማቆም ይሞክራሉ:: ኤርትራ የሚቃወሙ የኢት ህዝብ ጠላቶች ናቸው በማለት ያልተፃፈ ነገር ማንበብ ይጀምራሉ::

ኧረ ስንቱ! በሚሞከረበ ጥያቄ ላይም የፖለቲካ ቀልዱና ወሸ፣ንብር የዛኑ ያህል ነው::"እየታገልን" እየታገልን "በትግሳችን"....እያሉ የገስ አርባታ ለኢት ህዝብ ያስተምራሉ::

የኢት የውጭ መመሪያ አምስቱ የታወቁት መርሆች ነው ተብሎ በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ላይ በግልጽ ሰፍሯል:: ከነኚህም አንዱ ባንዱ አገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ አለመግባት ነው ይላል:: ታዲያ ዛሬ ደርግ ውቅያኖስ ተሻገሮ የቻይና የኮሚዩኒስት ፓርቲ አድሃሪ ነው እያሉ ባንዱ ወገን ሲያወገዙ በሌላ ወገን አምስቱ ፕሪንስፕሎች መመሪያችን ነው ሲሉ ወሸ፣ንብር መንዛት አይደለም ወይ? የነሱስ ይሁን ደርግ ቀኝ ክበር በመታ ቅጥር የአድርባዮች አስክስታ አይገርም ወይ?

ያንዱ አገር አብዮት ሶሺያሊዝም ከገነባ በኋላ ሊቀለበስ አይችልም እያሉ የበራሽ ቲያሪ ያሰረጯሉ:: የቀረው ይቅርና ሊሆን የሚችል ነገር [ሃይፖተቲካል] ነው ብለው እንኳን ለ'ምሁር'አስተሳሰባቸው ክፍት ቦታ አልተውም:: ሊሆን የማይችል ነገር ከሆነ ደግሞ የማያስፈልግ ነገርና የሰውን አስተሳሰብ ሊያዳብር የማይችል ነገር ይሆንና በዚህ ጥያቄ ላይ መወያየቱ ጊዜን በከንቱ ማባከን ይሆናል ማለት ነው:: የኢት ህዝብ ለማምኘት ሲሉ አረሳቸውን ያደዱባሉ::



ለበራሽ ርእዮተ ዓለም የተገዛ ጭንቅላት ነፃ በሆነ መንገድ አስተሳሰቡን ሊያዳብር አይችልም::

ያለው የህዝብ ሚሊሽያ ህዝባዊ ሠራዊት ተብሎ ይጠራል:: ወደ እውነተኛው ህዝባዊ ሠራዊት እንዲለወጥ የሚያስፈልጉ ሃሳቦች ገና ምን ተደርገው ሲነሱ:: ስለንቃተ በተለይ ስለአመራሩ ጉዳይ ያነሳ"የማርያም ጠላት"ይበላል:: ይህ ሚሊሽያ በዚህ ዓይነት አመራር ውስጥ እስካለ ድረስ እንኳን በቅርብ ጊዜ በሩቅ ጊዜ ወዲያ ህዝባዊ ሠራዊትነት ለመለወጥ ያዳግተዋል::

በብሔር ጥያቄም ያለው ትርምስ አስቀድመን እንደጠቆምነው የመገንጠልን መብት ጠምሮ አለማወቁ ብቻ አይደለም:: በዚህም ደረጃ ስሬ ቅስቀሳ ማድረጋቸው ብቻ አይደለም:: በወረቀት ላይ ያሰፈሩትን እስከ እውቶኛሚ ድረስም ቢሆን የብሔረሰቦችን መብት መከዳታቸው ነው:: በደቡብ ያሉትን ጭቁን ብሔረሰቦች ከሚያስፈልገው በላይ ኤዳቸሁል በሚል የሀሰት ወንጀል በትምክህተኛ ፖሊስ እየተመቱ ናቸው::

በብሔረሰቦች ያስተዳደርና የነፃ አርምሻ ላይ ከሚገባው በላይ ኤዳቸሁል ብሎ ቅጥጥር ማድረግ በውቶኛሚ ደረጃ እንኳን የብሔረሰቦችን መብት አለማወቅ ነው:: ብሔረሰቦች የራሳቸውን እድል የሚወስኑት በራሳቸው ነው እንጂ ተወካይ አድርባዮች ሊሆኑ አይችሉም:: አድርባዮች የብሔረሰቦችን መብት እስከአውቶኛሚም ቢሆን አናውቃለን ይላሉ ገን ይህን መብት ሥራ ላይ የምናውለው እኛ አድርባዮች እንጂ ጭቁን ብሔረሰቦች አይደሉም ይላሉ:: ቅጥ ያጣ ትርምስ!

አብዮት የሚለውንም ቃል እንደ መጥፎ ነገር የሚቆጥሩ ጭቁኖችም ጥቂቶች አይደሉም:: በአብዮት ሥም ሲገፈፋ እንጂ ሲያልፍላቸው አላዩም:: በአብዮት ስም የፀረ—አብዮት ስጠቁናቸው እንጂ እነሱ አልተዝናኑም:: አልተነፈሱም:: በቀላሉ የፀረ—አብዮት ድርጊት አብዮት ተብሎ ሲጠራ ያዩና ያዳመጡንቃተ ከፍ ያላለ ጭቁን አብዮትን ቢጠሉና የፀረ—አብዮት ሃይል ወይም መሃል ሰፋሪ ቢሆን አይደንቅንም ነው:: እየሆነም ነው::

በበኩላችን እስከሁን ድረስ ምስሌያችን በማንሳት በኢት ውስጥ የሚደረገውን ወሸ፣ንብር ለማስታወስ ሙከራ አደርገን እንጂ እያንዳንዱን ወሸ፣ንብር አልጠቀስንም:: ወይም በጠቀስናቸው ወሸምብሮች ላይ ትችት አልከፈትንም:: መችም ደህና ጊዜና ጉልበት አገኘተን በወሸምብሮች ላይ ትችት መከፈታችን አይቀርም::

## የቀኝ አድርባይነት እንዴት ሊጠናከር ቻለ?

ቀደም ብለን እንደጠቀስነው የአድርባዮች መጠናከር በቀጥታ ከመንግሥት ጋር ካላቸው ግንኙነትና የህዝቡ የንቃት፣የድርጅትና የትጥቅ ዝግጅት በበቂ ካለመሟላትና እንዲሁም የሰፊው ህዝብ በዚያ በተወሰነ ጊዜ ካለው የዲሞክራሲ መብቶች ጋር የተያያዘ ነው፡፡

ዛሬ በኢት ውስጥ የቀኝ አድርባይነት መረኑን ለቆ እንደዚህ ሊስፋፋ የቻለበት አራት ዋና ዋና ምክንያቶች አሉ፡፡ ይህ ማለት ሌሎች ምክንያቶች የሉም ለማለት አይደለም፡፡ ያም ሆነ ይህ:—

1 — በአሁኑ ጊዜ የቀኝ አድርባዮች ከመንግሥት ጋር ያላቸው ግንኙነት ግለትም ዛሬ የቀኝ አድርባይነትን መስመር በግንባር ቀደምነት የሚያራምደው ደርግ|ሰደድ በመሆኑ ይህንን መስመር ለማራመድ በእጁ ውስጥ ያለውን የፖለቲካ ስልጣን በመጠቀም በህዝቡም ዘንድ ተቀባይነት ባይኖረውም በቁጥጥሩ ስር ያሉትን የጭቆና መሣሪያዎች በሙሉ እየተጠቀመ በወጣለት ፀረ—ዲሞክራሲያዊ መንገድ በጉልበት ይህን መስመር ሊያራምድ ስለሚችልና በገበርም በዚሁ አይነት መልክ እየሠራ ስለሚያራምድ፡፡

2 — የሰፊው ህዝብ የዲሞክራሲ መብቶች ታፍነው በመያዛቸው ይህን የቅልበሳ መስመር በግልጽ ለማጋለጥ ባለመቻሉ፡፡ የቀኝ አድርባዮች የሰፊውን ህዝብ የዲሞክራሲ መብቶች አፍነው እንዳይለቀቁ የሞት የሽረት ትግል የሚያካሂዱት በዚህ ፀረ—አብዮት አቋማቸው በአንድ ጊዜ ተጋልጠው የኢህአፓ አድል እንደሚያጋጥማቸው ጠንቅቀው ስለሚያውቁት ነው፡፡

3 — የህዝቡ የንቃት፣ የድርጅትና የትጥቅ ዝግጅቶች አሁንም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ስለሚገኙ የቀኝ አድርባዮችን አጋልጦ ለመደምሰስ ለጊዜው የሰፊው ህዝብ ዝግጅት በቂ ስላልሆነ፡፡

4 — የቀኝ አድርባዮች በአለም አቀፍ ደረጃ ባላቸው የሞራልና የማቴሪያል እርዳታና ድጋፍ በተለይ ይህን ሁኔታ የኢት ጭቁን ህዝቦችና ሃቀኛ አብዮታዊያን በቅጡ ማጤን ይኖርባቸዋል፡፡ እንዲያውም በኢት ውስጥ የቀኝ አድርባዮች የልብ ልብ አገኝተው በደንብ የተጠናከሩት ከውጭ የማቴሪያል እርዳታ በገፍ ማግኘትና የፖለቲካ ድጋፍ ማግኘት ከጀመሩ ወዲያ ነው፡፡ በተለይ የፀረ—አብዮት አቋማቸውን በግልጽ



አውጥተው ማሳየት የጀመሩት በግንቦት ወር በሰፊው ከውጭ እርዳታ መገኘት ከተጀመረ ወዲህ ነው፡፡

አንባቢ እዚህ ላይ የቀኝ አድርባዮች ለምን ከግንቦት በፊት የውጭ እርዳታ አላገኙም ብሎ ይጠይቅ ይሆናል፡፡ የቀኝ አድርባዮች ከኢህአፓ ጋር ይካሄድ በነበረው የርእዮተ አለም ትግል ውስጥ ያስተጋቡ የነበሩት መስመር ፍጹም ማርክሲስት ሌኒኒስት የሆነውን የመኢሶንን መስመር ስለነበረ፣ አራቱ የደርግ መሰስተኛ ፕሮግራም እነዚህ አድርባይ ድርጅቶች ኢህአፓን ለመታገል ብቻ እንጂ በደንብ አምነውበት ባይሆን እዚያም እዚህም ይጠቃቀሷቸው የነበሩት የማርክስ፣ የሌኒን፣ የስታሊንና የማኦ አብዮታዊ ጥቅሶች ባጠቃላይ እነዚህ ሁኔታዎች በአለም አቀፍ ደረጃ አድርባይ ሃይሎችን ክፉኛ አወናብደቻቸው ስለነበርና የቀኝ አድርባዮች በወቅቱ ለውጭ ተመልካች ይሰጡት ለነበረው የተሳሳተ መልክ እውነትም አብዮታዊ ማሌ ድርጅቶች መስለው ስሳልታያቸው በሙሉ እምነት ሊደግፏቸው አልቻሉም፡፡ በየአገሩ እንዳሉ እንደሌሎች ተለካሽ የቀኝ አድርባይ ፓርቲዎች በቁጥጥራቸው ስር ሊያደርጓቸው የሚችሉ መስሉ አልታያቸውም ነበር፡፡''ወዛደር አለም አቀፋዊነት''እናምናለን የሚሉት ሃይሎች የኢት ጭቁን ህዝቦች አብዮት እንደዚ በውስጥና በውጭ ጠላቶች ተወጥሮ በተያዘበት ወቅት በኢት አብዮት ላይ ይዘምት የነበረውን የሶማሊያ ባሬን አሻንጉሊት መንግሥት ይረዱ እንደነበረ የዛሬዎቹ የቀኝ አድርባዮች በዘነጉት የኢት ጭቁን ህዝቦችና ለአብዮቱ በሃቅ የቆሙ ተራማጆች ምን ጊዜም አይዘነጉትም፡፡ በሌላም ወገን አሁንም ''ለወዝ አደር አለም አቀፋዊነት''''ለሶሻሊዝም ለዲሞክራሲና ለፍትህ''ቆመናል የሚሉት በአለም አቀፍ የደርግ ደጋፊዎች የደርግ|ሰደድ ቀኝ አድርባዮች አብዮታዊያን ማርክሲስት ሌኒኒስቶችን፣አገር ወዳዶችን፣ ዲሞክራቲክ ሃይሎችን በገፍ ሲጨፈጭፉ፣ ሲያስሩ፣ ሲያባርሩ እነዚህን አድሃሪ ሃይሎች በአለም አቀፍ ደረጃ ተራማጅ አስመስሎ ለማቅረብ የሚያደርጉትንም ጥረት የኢት ጭቁን ህዝቦችና ሃቀኛ አብዮታዊያን ምን ጊዜም ሊረሱት አይችሉም፡፡

ገራም ነፈሰ ቀኝ ምንም እንኳን የቀኝ አድርባዮች ከላይ በጠቀስናቸው ምክንያቶች ለጊዜው ተጠናክረው ቢገኙም ቅሉ በመጨረሻ እንደ ኢህአፓ በሰፊው ህዝብ ክንድ እንደሚደመሰሱ ለአንዲት ሰከንድ እንኳን አንጠራጠርም፡፡

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር
መጽሔት አዘጋጅ ቦርድ
The Ethiopian Students Union in Europe
Editorial Board

## ማሳሰቢያ

ውድ አንባቢዎቻችን ፤

የሙሉን ንቅናቄ ከወጣት ሆኖ ቦርቦር ለማስከም ያደረገው ጥረት ስላልተሳካለት እርሱን በንቅናቄያችን ያገለለው ፀረ ሕዝብ ቡድን ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ጥልቅ በላይ ሰፊው ሕዝብ ጋር በመሰለና ያለምንጊዜም ያለው ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ፊውዳሊስት ትግሉ ሊያሳዩ በሚረው ማህበራችንና [illegible] ዘንድሮ [illegible] ያስተጋቡትን ንቅናቄ በመንገድ የሰፊውን ሕዝብ ወገኖች ትግል ሊያስተጓጉሉ በሚሬት ጉልበተኞች የተቀደሰ ማህበራት መጽሔት በላይ የሰፊው ሕዝብ [illegible] ማስተማሪያ መ [illegible] ህገ ወጥ በቃሉ በንቅናቄ በትግላችን ስም መጽሔት [illegible] የሆነ ፀረ ሕዝብ ጉዳይ ዓላማ ማህበራችን አንዱም ንቅናቄ ትግላችን [illegible] ላይ የገለ ብተረፈቸ ስም ተመቅ ፀረ ሕዝብ ፖለቲካን ለመበረዝ ነው [illegible] ህጋዊ ሆኖ የሚያውን የኢትዮጵያ ተማሪዎችና ተራማጆች አንድነት የሚያ [illegible] ሰላም ሆኖ ወዘተገበር በመገዛት ለማፈን ነው፡፡ይህም እንደማይሳካ [illegible] ለማንኛውም የሚጠይቀው መጽሔት አዘጋጅ ቦርድ አድራሻ/ማለትም P.O.BOX 3198
10364 STOCKHOLM - SWEDEN ያለ ይህ የዓለም ዓቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር እያስተነ የሚያመለከት ነገ የማህበራችን መጽሄቶች ስም የያዘ መጽሄት ወዘተ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር መጽሄት አለመሆኑ ነውን አንባቢዎቻችን እንድታውቁልን እንጠይቃለን፡፡ለእነዚህ አይነት መጽሄት ተጠያቂው [illegible] ዓይነ ፈንረጅን " በሚባል ስም የታወቀው የነ አስተወሰን — ወንገሺ [illegible] [illegible] ነው፡፡

ከፋሽስቶችና ለምርኮኞች ከፊውዳሊዝምና ከአምፔሪያሊዝም ጋር ይወድቃሉ!
የአውሮፓ እና ኢትዮጵያ ተራማጆች አንድነት ይኑር!
ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው!

በአሌቶማ መጽሄት አዘጋጅ ቦርድ